ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 207 መጋቢት 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia






## “ክልሎችን በአፈጻጸምና በውጤት ማቀራረብ ቀጣይ ተልዕኳችን ነው”

- አቶ አደም ፋራህ
በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ክልሎችንና ከተማ አስተዳደሮችን በግንዛቤ፣ በአፈጻጸምና በውጤት ማቀራረብ የቀጣይ ተልዕኳችን ነው ሲሉ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማስተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ ገለጹ፡፡

“ክልሎችን በአፈጻጸምና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “እንደመንግሥት ‘ስታርት አፖችን’ መደገፍ ኢንቨስትመንት እንጂ ርዳታ አይደለም”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- እንደ መንግሥት በፈጠራ ላይ የተመሰረተና የመፍትሔ ሃሳብ ያላቸውን ‘ስታርት አፖች’ መደገፍ ኢንቨስትመንት እንጂ ርዳታ አይደለም የሚል እሳቤ አለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ። “የኢትዮጵያ ስታርት አፕ ብሔራዊ ሁነት” በዓድዋ መታሰቢያ ትናንት ተካሂዷል።

በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር)፤ “ስታርት አፕ” ማለት ማንኛውም ሥራ ሳይሆን በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ፣ ገቢ የሚያመነጭ እንዲሁም ለአንድ ጉዳይ መፍትሔ ያለው አዲስ የሥራ ፈጠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ስታርት አፖችን መደገፍ ከቻልን የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፣

“እንደመንግሥት‘ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## “ኢትዮጵያ ከመጋቢት እስከ መጋቢት ታሪካዊ አሻራ በማኖር ብልጽግናዋን እውን ከማድረግ የሚያቆማት ኃይል የለም”

-ለገሰ ቱሉ(ዶ/ር)
የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር

ገጽ 4

# መሠረታዊ ለውጥ የሚሻው አገልግሎት

**ዘላለም ግዛው**



**ዜና ሐተታ**

በቅጥር ግቢው ሰፊ መጋዘን መሳይ አዳራሽ አለ፡፡ በስማቸው ፊደል ተራ ተሰባስበው የስማቸውን መጠራት በጉጉት የሚጠባበቁ ደንበኞች በግቢውም በአዳራሹም በርካታ ናቸው፡፡

ለተሰብሳቢዎቹ ድምጻቸውን ጎላ ያደረጉ የአገልግሎቱ ሠራተኞችም በየተራ ስም ይጣራሉ፡፡ ጉዳያቸውን ያሳኩ ፓስፖርታቸውን ይዘው ፊታቸው ሲፈካ፤ ተራ ያልደረሳቸው ደግሞ እየተማረሩ ሲጠባበቁ ይታያሉ፡፡

አናት የሚበሳውን ፀሐይ ተቋቁመው ተራ የሚጠባበቁ አዛውንቶች፣ ሕፃናት የያዙ ወላጆች እና ነፍሰጡሮችን ጨምሮ ሲጉላሉ የሚስተዋልበት ትዕይንት ጎተራ እና በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አካባቢ የሚገኘው የኢምግሬሽንና የዜግነት አገልግሎት ግቢ ውስጥ ተመልክተናል፡፡

ጉዳይን ፈጽሞ መመለስ እንደልዩ ዕድል የሚቆጠርበት

መሠረታዊ ለውጥ ... ወደ ገጽ 3 ዞሯል




# የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግል ዳታ ጥበቃ ረቂቅ አዋጅን አጸደቀ

## - አዋጁ የግል ዳታ ጥሰት እንዳይፈጸም ለመቆጣጠር የሚያስችል ነው

**ዳግማዊት አበበ**





ዶ/ር ነገሪ ሌንጮ

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግል ዳታ ጥበቃ ረቂቅ አዋጅን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ አጽድቋል፡፡ አዋጁም ግል ዳታ ጥሰት እንዳይፈጸም ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑ ተገልጿል፡፡

ምክር ቤቱ 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 20ኛ መደበኛ ስብሰባውን በትናንትናው እለት ሲያካሂድ የግል ዳታ ጥበቃ ረቂቅ አዋጅን በአንድ ተቃውሞና በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል ፡፡

ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳቡን ሰው ሀብት ልማት፣ ሥምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር) ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ ረቂቅ አዋጁን ለመመርመር እና በጥልቀት ለማየት ጥረት ተደርጓል፡፡

አዋጁ ጠንካራ የግል ዳታ ጥበቃ ሥርዓት እንዲፈጠር ለማድረግ ወሳኝ መሆኑንና የግል ዳታ በሚሰበሰብበትና በሚቀናበርበት ወቅት የግል ዳታ ጥሰት እንዳይፈጠር ለመቆጣጠር የሚያስችል በመሆኑ አዋጁን ማውጣት አስፈላጊ ሆኗል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

አዋጁ የግል ዳታ ጥበቃን በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን የሚያስቀምጥና የግል ዳታ ጥበቃ ተቆጣጣሪ ተቋምን የሚሰይም ይሆናል ብለዋል፡፡

ነገሪ (ዶ/ር)፤አዋጁ ከዳታ ማቀናበር ሥራዎች ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለመቀነስ እና በኢትዮጵያ የግል ዳታ ጥበቃ ሥርዓት ዓለም አቀፋዊ ደረጃዎችንም በጠበቀ መልኩ ለመገንባትም ወሳኝ መሆኑን ገልጸው፤ በሕገመንግሥት ውስጥ ያሉ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችም እንዲጠበቁ የሚኖረው ሚና ከፍ ያለ መሆኑን አንስተዋል ፡፡

የምክር ቤቱ አባላት በበኩላቸው፤አዋጁ ማሻሻያዎች ሲደረጉለት ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ የሚለው ወጥቶ በዳታ ላይ ለመወሰን ያልደረሰ ታዳጊ በሚል መተካቱ ከሕገ መንግሥቱ ጋር የሚጣረስ መሆኑን አንስተዋል፡፡ የሚወጡ አዋጆች ከሌሎች ሕጎች ጋር መጣጣማቸውን ትኩረት ተሰጥቶት መታየት እንደሚገባ ጠይቀዋል፡፡

በማሻሻያው የግል ዳታ ጥሰት የፈጸመ አካል መቀጮ በእጥፍ እንዲጨምር ባደረጉ ምን ያህል አቅምን ያመዛዘነ መታየት አለበት ያሉት የምክር ቤቱ አባላት፤ ይህም ከሕግና ሙያ አንጻር ሊታይ ይገባዋል ብለዋል፡፡

ለምክር ቤት አባላት በሰጡት ምላሽ ነገሪ (ዶ/ር)፤ አዋጁ የግል ዳታ ላይ መወሰን የማይችሉ ብሎ ያስቀመጣቸው ከ16 ዓመት በታች ያሉ ዜጎችን ነው፡፡ ይህም ከሕገ-መንግሥቱ ጋር የሚጣረስ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁን ለማጽደቅ ረጅም ጊዜ መውሰዱን የተናገሩት ሰብሳቢው፤ ቅጣቱ እጥፍ የተደረገውም አሁን ያለው ምንዛሬና ከዓመታት በፊት የነበረው የማይመጣጠን በመሆኑ ልዩነቱ ሊሰፋ ችሏል ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የግል ዳታ ጥሰት የሚፈጽሙ አካላትን አስተማሪ በሆነ አግባብ ለመቅጣትም ያለመ መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

ቀደም ሲል በረቂቅ አዋጁ ላይ በበርካታ የሕግ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ የታየና ሕዝባዊ ውይይቶችም የተደረገበት መሆኑን ጠቁመዋል ፡፡



# አዋጁ ሃይማኖታዊ በዓላት አከባበርና የጋራ ድሎችን እውቅና ለመስጠት ያስችላል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የሜዳይ፣ ኒሻን ሽልማት አዋጅ የሃይማኖት እና የድል በዓላትን አከባበር እንዲሁም በጋራ የተሳኩ ድሎችን እውቅና መስጠትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን በሚኒስቴር ዴኤታ ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የሕግ አማካሪ አለምአንተ አግደው ገለጹ፡፡

የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የሜዳይ፣ ኒሻን ሽልማት ረቂቅ አዋጅ ላይ የአስረጂ መድረክ አካሂዷል፡፡

በአስረጂ መድረኩ ላይ የተገኙት የሕግ አማካሪው አለምአንተ፤ የሃይማኖት እና የድል በዓላትን አከባበር፣ የማህበራዊ እሴቶችን እና በጋራ ያሳካናቸውን ድሎች እውቅና መስጠትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በተቋም ግንባታ እና በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ገልታ፣ ለሀገር አስተዋጽኦ ያደረጉ ሰዎችን በመሸለም ሌሎች የሚበረታቱበት ሥርዓት የመፍጠር እሳቤ እንዳለው አስገንዝበዋል፡፡ ትውልድን ለማነሳሳት እና አርአያ በመሆን ሌሎች እንዲነሳሱ በማድረግም ፋይዳው የጎላ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

ለቋሚ ኮሚቴው ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት በፍትህ ሚኒስቴር የሕግ ጥናትና ማርቀቅ ዳይሬክተር አዲስ ጌትነት በበኩላቸው፤ በሀገር፣ በአፍሪካ ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ዘርፎች የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ እና ሀገራዊ እውቅና ሊሰጣቸው የሚገቡ ግለሰቦችና ድርጅቶች ተገቢውን ዕውቅና ለመስጠት የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በአጠቃላይ ለሰው ልጆች የሚጠቅም የላቀ ተግባር የፈጸሙ ሰዎችን ወይም አካላትን እውቅና በመስጠት ሌሎች የእነሱን አርአያነት እንዲከተሉ ዓላማ ያደረገ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

በዋናነት የሜዳይ ኒሻን ሽልማት ማን እንደሚሰጥና እንደሚያቀርብ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 71 መሰረት የተቀመጠ መሆኑንም በመጠቆም፤ አሰራሩን የበለጠ ለማስፈጸም በኮሚቴ ደረጃ የመለየቱን ስራ ለመስራት እንዲያስችል መቀመጡን ጠቁመዋል፡፡

የሜዳይ፣ ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ እና ንዑሳን ኮሚቴዎች የተሻለ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን እንዲያገናዝቡ ተደርጓልም ብለዋል፡፡ በቁጥር፣ በስብጥር፣ ምን አይነት ሙያ እንደሚኖራቸው በመመሪያ እንዲወሰን በሚል በአዋጁ የተመላከተ መሆኑንም ነው የጠቆሙት፡፡

ሽልማቱ በሀገራዊ አውድ ውስጥ የሚፈጸም ቢሆንም፤ ክልሎችም በክልል አውድ ውስጥ የአንድን ክልል ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ መስጠት የሚያስችላቸው መሆኑንና ለተሸላሚው ካበረከተው ፋይዳ አንጻር ሁለት ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እንደሀገር ሊሰጥ ይችላል፡፡ በተለየ መልኩ ለክልሉ ላይ የፈጠረው ነገር ካለ የሚሰጥበት አግባብ ይኖራልም ነው ያሉት፡፡

በሀገር በተለያዩ መስኮች የላቀ ስራ የሰሩ ግለሰቦችን እና ሌሎች አካላትን እውቅና በመስጠት ሌላው ማህበረሰብ የእነርሱን አርአያ እንዲከተሉ የሚያበረታታ መሆኑ በረቂቅ አዋጁ ተቀምጧል፡፡ የስራ ፈጠራ እንዲስፋፋ እና ሁለንተናዊና ቀጣይነት ያለው ልማት ለማስመዝገብ አስፈላጊ መሆኑም ተመልክቷል፡፡

በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ዘርፎች እንዲሁም በምርምር፣ በትምህርት፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በህክምና በስነጥበብ፣ በስነጽሁፍ፣ በባህል፣ በአካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች ለሀገር እድገት ተጨባጭና የላቀ ተግባር ለፈጸሙ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች ክብር እና እውቅና መስጠት አስፈላጊ መሆኑም ነው የተቀመጠው፡፡

# በድሬዳዋ የሕግ ታራሚዎች የበደሉትን ማህበረሰብ ለመካስ እየሠሩ ነው

**ተስፋ ፈሩ**



ረዳት ኮሚሽነር ወንድሙ ደበላ

ድሬዳዋ፡- በድሬዳዋ ሁሉ አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት የሚገኙ የሕግ ታራሚዎች የበደሉትን ማህበረሰብ ለመካስ የሚያስችላቸውን ስራ እየሰሩ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የድሬዳዋ ሁሉ አቀፍ ማረሚያና ማረፊያ ቤት ዳይሬክተር ረዳት ኮሚሽነር ወንድሙ ደበላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ በስድስት ማህበራት የተደራጁ ታራሚዎች የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ በማቅረብ የበደሉትን ማህበረሰብ የሚክሱበት ዕድል አግኝተዋል።

በታራሚዎቹ የሚመረቱት ብሎኬት፣ ፈሳሽ ሳሙና፣ የኤሌክትሪክ ምድጃ፣ የፍራፍሬ ጭማቂ እና የባህል አልባሳት ከድሬዳዋ አልፈው ጅግጅጋ እና ጭሮ ድረስ እየተላኩ እንደሚገኙም ገልጸዋል።

በሳንቡሳ ምርት ተደራጅተው በ6ሺ. ብር ካፒታል ስራ የጀመሩ ታራሚዎች 200 ሺ. ብር እንዲሁም ፈሳሽ ሳሙና አምራች ታራሚዎች ከ35 ሺ. ብር ካፒታል ተነስተው 300 ሺ. ብር ማስመዘገባቸውን ጠቁመው፣ "ይሄን የምናደርገው ታራሚዎች የበደሉትን ማህበረሰብ እንዲክሱ እና ገቢ አግኝተው ከማረሚያ ቤት በሚወጡበት ጊዜ በተማሩበትና በሰለጠኑበት ሙያ የራሳቸውን ስራ መጀመር እንዲችሉ ነው" ብለዋል፡፡

በማረሚያ ቤቱ ከሚገኙት ታራሚዎች ከፊሉ በተለያዩ የልማት ስራዎች ላይ ተሰማርተው እንደሚውሉ ጠቁመው፣ ታራሚዎች ምርታቸውን በቀጥታ ለህብረተሰቡ ማድረስ እንዲችሉ የመሸጫ ቦታ ሼድ ቢመቻችላቸው ይበልጥ ውጤታማ ይሆናሉ ነው ያሉት።

ማረሚያ ቤቱ እየሰራ ያለው ስራ ታራሚዎች ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀሉ የሰው እጅ እንዳያዩ ከማድረግ ባለፈ፣ ሰው ከሰራ ሀብት ማፍራት ይችላል የሚል እምነት እንዲይዙና በአቋራጭ ለመክበር ከሚደረግ ህገወጥ እንቅስቃሴ እንዲቆጠቡ የሚያደርግ ነው ያሉት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ ብዙዎች ከማረሚያ ቤቱ ወጥተው የራሳቸውን ፀጉር ቤት እንዲሁም ፈሳሽ ሳሙና እና ብሎኬት ማምረቻ እንደከፈቱ ተናግረዋል።

አርአያነት ላላቸው ታራሚዎች በቀጣዩ 2017 ዓ.ም መንጃ ፈቃድ ማስተማር ለመጀመር መታቀዱን ያነሱት ረዳት ኮሚሽነሩ፤ ማረሚያ ቤቱን የኢንዱስትሪ ማዕከል የማድረግ ህልም አለን። ለዚህም ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ፣ ከከተማዋ ቴክኒክና ሙያ ኤጀንሲ እና ከኢትዮ ጣሊያን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርመን በትብብር እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

በማረሚያ ቤቱ የሚገኘው ሰፊ የሰው ጉልበት ወደ ምርት መቀየር አለበት የሚል እሳቤ ይዘን እየተንቀሳቀስን ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ከአረማያ ዩኒቨርሲቲ ጋር በከተማ ግብርና ላይ በጋራ ለመስራት በሂደት ላይ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

ከማረሚያ ቤታችን የሚወጡ ታራሚዎች በስነምግባራቸው አንቱ የሚባሉ ባለሙያዎች እንዲሆኑ ስለምንፈልግ በቀጣይም የተሻለ ስነምግባር ያላቸውን ታራሚዎች መልምለን የተለያዩ ስልጠናዎችን በመስጠት ትክክለኛ የእውቀት መፍለቂያ መሆናችንን ለማስመስከር እንሰራለን ሲሉም አክለዋል፡፡

ማረሚያ ቤቶች የመንግስት ብቻ አይደሉም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ዜጎች፣ የተለያዩ ተቋማትና ባለሀብቶች አብረዋቸው እንዲሰሩ ጠይቀዋል።

ማህበረሰቡም ማረሚያ ቤት የሚገቡ ሰዎች ተለውጠው እንደሚወጡ በማመን እንዲደግፉቸውና ከጎናቸው እንዲቆም ጥሪ አስተላልፈዋል።

ዜና



# ‹‹ፊቼ-ጫምባላላ የፍቅር የአብሮነትና የመተሳሰብ ተምሳሌት ነው››

\- አቶ ደስታ ሌዳሞ
የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ፊቼ-ጫምባላላ የፍቅር፣ የሰላም፣ የአንድነት፣ የአብሮነትና የመተሳሰብ ተምሳሌት መሆኑን የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ገለጹ፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ ፊቼ-ጫምባላላ በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት እንዳሉት፤ የሲዳማ ሕዝብ በርካታ ባህሎችና ትውፊቶች ባለቤት ሲሆን የዘመን መለወጫ ፊቼ-ጫምባላላ አንዱ ነው። በዓሉም የፍቅር፣ የሰላም፣ የአንድነት፣ የአብሮነትና የመተሳሰብ ተምሳሌት ነው፡፡

ፊቼ-ጫምባላላ በዓል ለሕዝባችን የጥበብ ጥግ፣ ለሀገራችን ኩራትና እንቁ የባህላዊ ቅርስ ነው ያሉት አቶ ደስታ፤ ሲዳማ የራሱ የሆነ ጊዜን፣ ወቅትንና ዘመንን የሚቀምርበት ባህላዊ እውቀትና ጥበብ ያለው ሕዝብ ሲሆን፣ ይህን ባህላዊ እውቀቱንና ጥበቡን ከትውልድ ወደ ትውልድ እያሸጋገረ ለዚህ ትውልድ አድርሶታል ብለዋል።

እንደ ርእሰ መስተዳድሩ ገለጻ፤ የሲዳማ አባቶች (አያንቶዎች)ባህላዊ የስነ ፈለክ እውቀትና ጥበባቸው የረቀቀ ሲሆን የሰማይ ከዋክብትን የፀሐይንና የጨረቃን ህብራዊ ውህደትንና ተናጠላዊ አንድምታን በመመርመር የሲዳማን የቀን አቆጣጠር ካላንደር ፈጥረዋል፡፡

አብዛኛውን የዓለማችን ሕዝቦች ንቃተ ኀሊናቸው ባላደገበት ዘመን ቀደምት የሲዳማ አባቶች የሰማይን ተፈጥሯዊ ምንነት፣ የምድርን አቀማመጥ፣ የከዋክብትንና የጨረቃ ሥርዓትና ውሁደት መርምረውና አጥንተው ለዛሬው ትውልድ ይህን የቀንና የጊዜን መለኪያ ባህላዊ ጥበብ አድርሰዋል ብለዋል።

የሲዳማ ባህላዊ የቀን አቆጣጠር ጥበባዊ እሴት ትንታኔ በዓለም አቀፍ ቅርስነት መመዘኛዎች የሚመጥን ሆኖ በመገኘቱ በዩኔስኮ ከማይዳሰሱ ቅርሶች አንዱ ሆኖ መመዝገቡን ጠቅሰው፤ በዚህም የዓለም የጋራ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ ከሚደረግላቸው እና እውቅና ካገኙ ዓለም አቀፍ ቅርሶች አንዱ ለመሆን በቅቷል ነው ያሉት።

ፊቼ -ጫምበላላ በዓል ለተፈጥሮ እፅዋትና ስነ ምህዳር ልዩ እንክብካቤና ጥበቃ የሚያደረግ፣ የሴቶችና ሕፃናት መብት የሚከበርበት፣ ለደን፣ ለአፈና ለውሃ ጥበቃ እንዲሁም ለተፈጥሮ የሚሰጠው ክብር የላቀ መሆኑ በቅርስነት እንዲመዘገብ እንዳስቻሉትም ጠቁመዋል፡፡

በዓሉ ሲከበር ቂም፣ ቁርሾና በቀል ይዞ ወደ አዲስ ዘመን መሻገር ስለማይፈቀድ የሲዳማ ሕዝብ በሁሉቃ ሥርዓት ቂም፣ ቁርሾና በቀሉን በይቅርታ የሚያወርድበት በዓል መሆኑን አስታውሰው፤ የተጣላ የሚታረቅበት የይቅርታ፣ መቻቻልና አብሮነት የሚጎለብትበት፣ ፍቅርና መተሳሰብ የሚሰፍንበት ነው ብለዋል።

ፊቼ- ጫምባላላ ለሲዳማ ብሔረሰብ ተወላጅ ብቻ ሳይሆን አብሮ በሚኖረውም ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ እንድምታ የሚሰጠው መሆኑን ገልጸው፤ ሕዝባዊ ፍቅር የሚገለፅበት የተጣሉ የሚታረቁበት እንዲሁም የሰላምና የልምላሜ መገለጫም ጭምር ሆኖ ይቆጠራል ሲሉ ገልጸዋል ።

የሲዳማን ሀገር በቀል እውቀትና የብሔሩን ባህላዊ የስነ ከዋክብት ጥናት ለዓለም ሕዝብ የተዋወቀበት ስለሆነ ለቱሪዝም ኢንዱስትሪያችን መበልፀግ የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል ያሉት አቶ ደስታ፤ የሲዳማ ብሔረሰብ በዓሉን የሚያከብረው ያለው ለሌለው በማካፈል፣ በመረዳዳትና በመተሳሰብ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

አሁንም ይህን አኩሪ ባህላዊ ትውፊት ለማጉላት በዓሉን የተቸገሩ ወገኖችን በመደገፍና በመርዳት፣ የአካባቢያችንን ሰላም በመጠበቅ ማክበር እንደሚገባ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ከሳውድ አረቢያ 70 ሺህ ዜጎችን በዘመቻ መልክ ለመመለስ ዝግጅት እየተደረገ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በሳውድ አረቢያ ያለ መኖሪያ ፈቃድ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 70 ሺህ ዜጎችን በዘመቻ መልክ ለመመለስ ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሮ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲን በተመለከተ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር መገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች ትናንት ሳምንታዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ ነብዩ ተድላ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንዳሉት፤ በዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ በተለያዩ ሀገራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው የመመለስ ስራ እየተሰራ ነው፡፡

ሦስተኛ ምዕራፍ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው የማስመለስ ስራ በቅርቡ ይጀመራል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ መጋቢት 12 ቀን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳር ብርቱካን አያኖ የሚመራ 16 የፌዴራል ተቋማትን የያዘ ብሔራዊ ኮሚቴ ተዋቅሯል፡፡ ብሔራዊ ኮሚቴው በሳውድ አረቢያ ያለ መኖሪያ ፈቃድ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ 70 ሺህ ዜጎችን በዘመቻ መልክ የመመለስ ስራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዘመቻ መልክ ዜጎችን ወደ ሀገር ለመመለስ በቀን አራትና በሳምንት 12 በረራዎችን ለማካሄድ እቅድ ተይዟል ያሉት ቃል አቀባዩ፤በምዕራፍ ሶስት ዜጎችን ለማስመለስ የፌዴራልና የክልል ተቋማት በጋራ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

ቃል ቃባዩ፤ ወደ ሀገራቸው ከገቡ በኋላ ወደ ቀያቸው እስኪመለሱ ድረስ መጠለያ እየተዘጋጀ ነው፡፡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትም የሚጠበቅባቸውን ስራ እየሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዜጎችን ወደ ሀገር ከመመለስ ስራ ጋር በተያያዘ ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጣ ልዑካን ቡድን በያዝነው ሳምንት መጨረሻ ወደ ሳውድ አረቢያ በመሄድ ከሳውዲ አረቢያ ባለስልጣናት ጋር ውይይት እንደሚያደርግም ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ነብዩ ማብራሪያ፤ በዚህ ዓመት ከሳውድ አረቢያ በተደረጉ መደበኛ በረራዎች ስድስት ሺህ 993 ዜጎች ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ በመደበኛ በረራ የሚደረገው የመመለስ ስራ በሳውዲ እስር ቤት ከሚገኙና ወደ እስር ቤት እየገቡ ካሉ ዜጎች ቁጥር አንጻር አናሳ በመሆኑ በቀጣይ በዘመቻ መልክ የማስመለስ ስራ እንዲሰራ ተወስኗል፡፡

ዜጎች በሕገ-ወጥ ደላሎች ተታለው ወደ ሳውዲ አረቢያ፣ መካከለኛው የባህረ ሰላጤው ሀገራት፣ ወደ ደቡብ አፍሪካና ወደ ሌሎች ሀገሮች ይሄዳሉ፡፡ በዚህ ሂደት ቁጥራቸው ቀላል የማባይል ዜጎች ለሞትና ለእስር እየተዳረጉ ነው፡፡ መንግሥት ለዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲ ትኩረት በመስጠት በተለያዩ ሀገራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ያሉ ዜጎችን ወደ ሀገር ቤት ለመመለስና መልሶ ለማቋቋም በትኩረት እየሰራ ስለመሆኑም አቶ ነብዩ ገልጸዋል፡፡

ባለፈው ዘጠኝ ወራት 50 ሺህ 327 ዜጎች ወደ ሀገር እንዲመለሱ ተደርጓል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ከሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ጅቡቲ፣ ከኬንያ፣ ዚምባቡዌ፣ ግብጽ፣ ናይጀሪያና አልጄሪያ በድምሩ 20 ሺህ 455 ዜጎቻችን ተመልሰዋል፡፡ ከመካከለኛው ምሥራቅ 29 ሺህ 872 ዜጎቻችን እንዲመለሱ ተደርጓል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ከሳውዱ አረቢያ የተመለሱት ቁጥር ከሌሎች ሀገራት ከፍ ያለ ነው፡፡

ባለፈው ዓመት በአጠቃላይ ከ139 ሺህ በላይ ዜጎች ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ መደረጉን ጠቁመዋል፡፡

በተያያዘ ዜናም በትናንትናው ዕለት የአፍሪካ የቦክሲንግ ኮንፌዴሬሽን ጽህፈት ቤቱን በአዲስ አበባ ለመክፈት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ስምምነት አካሂዷል፡፡ በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ለጽህፈት ቤቱ ቢሮ ለመክፈትና በቀጣይ ለሚኖሩ ተጓዳኝ ስራዎች ድጋፍ እንደሚደረግ በአምባሳደር ብርቱካን አያኖ በኩል ማረጋገጫ ስለመሰጠቱ አቶ ነብዩ ገልጸዋል፡፡

# ስምምነቱ ለተገበያዮች ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠትና ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓትን ለመገንባት ይረዳል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከዘምዘም ባንክ ጋር ያደረገው ስምምነት ለተገበያዮች ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓትን ለመገንባት እንደሚረዳ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንድማገኝ ነገራ ገለጹ፡፡ የኢትዮጵያ ምርት ገበያና ዘምዘም ባንክ በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን ስምምነት በትናትናው ዕለት ተፈራርመዋል፡፡

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንድማገኝ ነገራ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ከባንኩ ጋር የተደረገው ስምምነት ፈጣንና ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት ለገዢና ሻጭ ከማቅረብ ባሻገር ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት ለመገንባት ይረዳል፡፡

ምርት ገበያው ለወጪ ንግድ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ 22 ምርቶችን ወደ ግብይት ሥርዓቱ በማስገባት ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ገዢዎች ክፍያ በወቅቱ ሲፈፀምላቸው ምርታቸውን በፍጥነት በመረከብ የገዙትን ምርት ለሚፈልጉት ዓላማ ለማዋል እንደሚያስችላቸውም ገልጸዋል፡፡

ሁሉም የገበያው ተዋንያን በዘመናዊ የግብይት ሥርዓት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የግብርና ምርቶች ግብይት ሥርዓትን በማዘመን፣ ግልፀኝነትንና መተማመንን በመፍጠር በኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ እንዲሆኑ የሚያስችልም ነው ብለዋል፡፡

ከባንኩ ጋር የተደረገው ስምምነት ተገበያዮች ግብይቱን ሲፈጽሙ የሚውስደውን ጊዜ ለማሳጠር እንደሚረዳ ጠቅሰው፤ ምርት ገበያው ዘምዘም ባንክን ጨምሮ ከ24 ባንኮች ጋር እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ምርት ገበያው ላለፉት 16 ዓመታት የኢትዮጵያ ገበያን ዘመናዊና ተደራሽ ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ገልጸው፤ የቢራ ገብስና የጨው ምርትን ወደ ግብይት ሥርዓቱ ለማስገባት በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል።

የግብይቱን በቀጥታ በኦንላይን ሥርዓት ለማካሄድ የመተግበሪያ ሶፍትዌር የማበልጸግ ሥራዎችን እያከናወነ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

የዘምዘም ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መሊካ በድሪ በበኩላቸው፤ ስምምነቱ ማህበረሰቡን በወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት በኩል አሳታፊ በማድረግ በምርት ገበያው እንዲገበያይ የሚረዳ ነው።

ባንኩ ሸሪዓን መሰረት ያደረገ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ መሆኑን ገልጸው፤ ከምርት ገበያው ጋር መስራት መቻሉ የባንኩ ደንበኞች ውጤታማ እንዲሆኑ ያስችላል ነው ያሉት።

ባንኩ አሁን ላይ የቅርንጫፎች ቁጥሩን ከ83 በላይ ማድረሱንም ጠቅሰው፤ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

# መሠረታዊ ለውጥ የሚሻው...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በዚህ ትዕይንት በዋና መሥሪያ ቤቱም ሆነ በቅርንጫፉ ግቢና ደጃፎቹ በርከት ያሉ ተገልጋዮች ምሬት ሲያሰሙ መስማት የተለመደ ነው፡፡

በርግጥ 24 ሰዓት የፓስፖርት ህትመትና በበይነ መረብ ምዝገባ ሥርዓት ተዘርግቷል፤ የአሠራር ሥርዓቱም በመጠኑ መሻሻል ታይቶበታል፤ ይሁን እንጂ አሁንም ከሕዝብ ፍላጎት ጋር የአገልግሎት አሰጣጥን ማጣጣም፣ ሙሉ አሠራሩንም ማዘመን ፣ ታትሞ የደረሰ ፓስፖርት እንዳለውም ቅልጥፍና ይፈልጋል ባይ ናቸው ተገልጋዮች፡፡

ለፓስፖርት እድሳት በአገልግሎቱ የተገኙት አስተያየት ሰጪ (ማንነታቸውን ለመግለጽ አልፈቀዱም) ለሁለት ወራት ተኩል ተቀጥረው ከስድስት ወራት ቆይታ በኋላ ፓስፖርታቸውን ማግኘታቸውን ይናገራሉ፡፡

‹‹መልእክት ደርሶኝ በቀጠሮዬ ቀን ብገኝም ዋናው መሥሪያ ቤት የማይገፋ ሰልፍ አጋጥሞኝ ነበር›› ሲሉም ያስታውሳሉ፡፡ ግፊያው የማይመች፣ የፀጥታ አስከባሪዎች ወከባና ዱላ እንደነበረበት በማስታወስም ያማርራሉ፡፡

ከሁለት ቀናት መጉላላት በኋላ ወደ ግቢው ለመግባት እንደቻሉ የሚጠቁሙት አስተያየት ሰጪዋ፤ 15 ቀናት ታገሱ ተብለው እንደመለሷቸው በተቀጠሩበት ቀንም አለመሳካቱን ይጠቁማሉ፡፡

አሁን ፓስፖርታቸውን መቀበላቸውን ይጠቅሱና፤ በበይነ መረብ ማመልከቱ የሰውን እንግልትና የተገልጋይን መጉላላት እስካላስቀረ፣ አሠራሩንም እስካላቀላጠፈ ድረስ ምንም ትርጉም እንደሌለው፣ የደረሰ ፓስፖርት እደላውን ቢያስተካክሉት የተሻለ መሆኑንም ይናገራሉ፡፡

‹‹ባጋጣሚ የደረሰኝ አዳራሽ ውስጥ ነበር፣ በየአቅጣጫው በጋራ ስለሚጠራ አይሰማም፣ ውጪም ተመሳሳይ እደላ በመኖሩና ከፍተኛ ሙቀት በመኖሩም ለተገልጋይ ምቹ አይደለም›› ሲሉም ይናገራሉ፡፡ በተለይ ከክፍለ ሀገር የሚመጡ ተገልጋዮች ሰልፍ እንዳለ ተጋንኖ እየተነገራቸው ለወረፋ እስከ አንድ ሺህ ብር በሚጠይቁ ደላሎች እንዳይታለሉ መጠንቀቅ እንዳለባቸውም ይመክራሉ፡፡

ለፓስፖርት እድሳት አገልግሎት ለማግኘት የተገኙት ሌላው አስተያየት ሰጪ፤ ‹‹ለሁለት ወር ቀጠሮ የተሰጠኝ ቢሆንም በተቀጠርኩበት ጊዜ አልደረሰልኝም፡፡ ዛሬ ተመስገን በጠዋት ወስጄለሁ፤ የደረሰኝ ባመለከትኩ በሦስት ወር ከ10 ቀኔ ነው›› ይላሉ፡፡

ባለቤታቸው አዲስ ለመውሰድ ጠይቀው ለስድስት ወራት ተቀጥረው በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙም ይጠቁማሉ፡፡

ኢምግሬሽን በተለምዶ ጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አካባቢ የመጀመሪያው ቀን ወረፋ ሳይደርሰኝ ተመለስኩ፡፡ በሁለተኛው ቀን ግን በአምስት መቶ ብር የቀጠርኩት ሰው ሌሊት ወረፋ ይዞ አስገባኝ፡፡ አሁን የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል አለው፡፡ ነገር ግን ከዚህም በላይ በተለይም የደረሰ ፓስፖርት እደላውን ማስተካከል ቢቻል ጥሩ ነው፡፡

ሌላው አስተያየት ሰጪ አዲስ ፓስፖርት ለመውሰድ ባመለከቱ በሁለት ወሩ መውሰድ ትችላለህ መልእክት እንደደረሳቸው፣ በማግስቱም ያለመጉላላት እንደደረሳቸው፣ ከዛም ቀደም ባሉት የዕረፍት ቀናት የሁለት ልጆቻቸውን ፓስፖርት መውሰዳቸውን ነው የሚያስታውሱት፡፡

ሰዓቱን ጠብቆ ለሚደርስ ተገልጋይ ወደ አገልግሎቱ ጊቢ ለመግባት ወረፋ አይቸገርም፤ ነገር ግን አንዳንዶች ባለማወቅ በጠዋት መጥተው የሚሰለፉ፣ ከፍለው ሌሊት ወረፋ የሚያስይዙ አሉ ይላሉ፡፡

አገልግሎት አሰጣጡን ከዚህ በላይ ማሻሻል ይችላል የሚሉት አስተያየት ሰጪው፤ የደረሱ ፓስፖርቶችን በጥሪ ከማደል ይልቅ አገልግሎት ፈላጊው ሳይጉላላና ጊዜውንም ሳያባክን በቀላሉ የሚያገኝበትን አሰራር መዘርጋት እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡

“ቁጭ ብሎ መልእክት የሚጠባበቅ ሰው ሁለት ዓመትም ሊፈጅ ይችላል” የሚሉት ደግሞ ካመለከትኩ አንድ ዓመት ሆኖኛል ያሉን ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አካባቢ በሚገኘው የአገልግሎቱ ቢሮ በር አካባቢ ያገኘናቸው ተገልጋይ ናቸው፡፡

ደንበኛው እስካሁን አልተጠራሁም፣ ወደ ግቢ ለመግባት ግን የነበረው ወረፋ ቀንሷል ፣አሁን ከመጣሁ አንድ ሰዓት አልሞላኝም፤ ነገር ግን ወደ ግቢው ልገባ ተቃርቤያለሁ ነው ያሉት፡፡ እስካሁን ሳይጠሩ መዘግየቱ ተገቢ እንዳልሆነም ነው የሚናገሩት፡፡

የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰላማዊት ዳዊት ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የኢሚግሬሽን ሪፎርም ከጀመረ ባለፉት ስድስት ወራት ከመግቢያ በር ጀምሮ የሙስና አሰራሮችን፣ ከደላሎች ጋር የነበሩ ሰንሰለቶችንና መሰል ስራዎችን የመበጣጠስ ሥራ ተሰርቷል፡፡

በተለያዩ ሕገ ወጥ ተግባር ተሰማርተው በተገኙ በ205 ሠራተኞች ላይ ከሥራ ከማገድ አንስቶ የተለያዩ ቅጣቶች ተጥለዋል፡፡ ከ53 በላይ የሚሆኑት በሕግ ጥላ ስር ሆነው ጉዳያቸውን እየተከታተሉ ናቸው፡፡

ፓስፖርት ውጭ ሀገር የሚታተም እንደመሆኑ የግዢ ሰንሰለቱን፣ የጉዞ ሁኔታውንና መሰል ተግባራትን በማስተካከል በስድስት ወራት ከአንድ ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ የፓስፖርት ደብተር ታትሞ ወደ ሀገር ቤት መግባቱንም ይናገራሉ፡፡

ግላዊ መረጃ ለማስፈር በቀን ሁለት ሺህ ይታተም የነበረውን በማሳደግ በቀን ከ10 ሺህ በላይ እየተሠራ ይገኛል፡፡ ብዙ ማተም ብቻ ሳይሆን እኩል ማሰራጨት በመፈለጋችን ትልቅ ችግር ተፈጥሮብናል፡፡ ሰው በተባለው ቀን እና ጊዜ መጥቶም አልወሰደልንም፡፡ 10 ሺህ ሰው ጠርተን የምንሰጠው ሶስት ሺህ ወይንም 30 በመቶ ነው፡፡

የስርጭት ቦታዎች ውስንነትም ሌላው ችግር ሆኖብናል የሚሉት ወይዘሮ ሰላማዊት፤ አሰራሩን ማሻሻል እንዳለብን አውቀን የተለያዩ ማእከላት ግንባታ እና አማራጮችን ለመጠቀም እየሰራን እንገኛለን ይላሉ፡፡

ሲስተሙ ይሰራል፣ ችግር የለበትም፡፡ በበይነ መረብ ለሚያመለክቱ እየቀጠረ ያለው ለሁለት ወራት ነው፡፡አገልግሎት አሰጣጡን በሚፈለገው መልኩ ያልተቀላጠፈው ሲስተሙ ሳይሆን መጠራቀሙ ያመጣው ችግር ነበረ ነው የሚሉት፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ አሁን ምንም አይነት ክምችት የለንም፡፡ እያተምን ያለነው አዲስ ያመለከቱትን ነው፡፡ አስፈላጊ ክፍያ ፈጽመው ቆይቶብናል የሚሉ ሰዎች የዘገየባቸው የጎደለ መረጃ ኖሮ ስለሆነ እንደገና ዋናው መስሪያ ቤት በመምጣት የጎደለውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

ሥራ የሚጀምረው ጠዋት ሁለት ሰዓት ነው፡፡ አሁን ሰልፍም፣ የተከማቸብንም የለም፡፡ ደንበኞች በጣም በቀላሉ ጉዳያቸውን መጨረስ ይችላሉ፡፡

ደንበኞች ራሳቸውን የኢምግሬሽን ሠራተኞችና ጉዳይ ፈጻሚ በማስመሰል በሚንቀሳቀሱ አካላት ሰለባ እንዳይሆኑ ሊጠነቀቁ ይገባል፡፡ እኛም በተቻለን መጠን እንዲህ አይነት ጥያቄ የሚያቀርቡትን እግር በእግር እየተከታተልን በሕግ እንዲጠየቁ ማድረጋችንን እንቀጥላለን ይላሉ፡፡

# “ኢትዮጵያ ከመጋቢት እስከ መጋቢት ታሪካዊ አሻራ በማኖር ብልጽግናዋን እውን ከማድረግ የሚያቆማት ኃይል የለም”

**-ለገሰ ቱሉ(ዶ/ር)**

***የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር***

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከመጋቢት እስከ መጋቢት ታሪካዊ አሻራ በማኖር፣ አብሮነትንና ትብብርን በማጎልበት፣ ማህበራዊ ትስስርና የዜጎች ክብርን በማጠናከር ብልጽግናዋን እውን ከማድረግ የሚያቆማት ኃይል እንደሌለ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ቱሉ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

የኢፌዴሪ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ለገሰ ተሉ (ዶ/ር)ያለፉት ስድስት ዓመታት የለውጥ ጉዞ፤ ወቅታዊ የሰላምና ደኅንነት ጉዳዮችና የበጋ ልማት ሥራዎች ላይ ባተኮሩ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት መግለጫ ሲሰጡ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያን ስኬቶች የሚያጣጥሉ፤ በአይናቸው እያዩ፣ በጆሯቸው እየሰሙ ዓለም ጭምር የመሰከረላትንና እውቅና የሰጣቸውን የልማት ትሩፋቶችን በዜሮ ለማባዛት የሚሞክሩ፤ የኢትዮጵያ መልማትና ለውጥ የእግር እሳት የሚሆንባቸው፤ የጨለማ ዘመን የሚናፍቁ አሉ፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ ከመጋቢት እስከ መጋቢት ታሪካዊ አሻራ በማኖር፣ አብሮነትንና ትብብርን በማጎልበት፣ ማህበራዊ ትስስርና የዜጎች ክብርን በማጠናከር ብልጽግናዋን እውን ከማድረግ የሚያቆማት አንዳችም ምድራዊ ኃይል የለም፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የሚመራው የለውጡ መንግሥት መሠረታዊ መርሆዎችን መነሻ በማድረግ ባለፉት ስድስት የለውጥና የብልጽግና ጉዞ ዓመታት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ በዚህም ሥር የሰደዱ የኢትዮጵያ ችግሮችን ከስር መሰረቱ ለመንቀልና የተረጋጋ አዎንታዊና ዘላቂ ሰላም ለመፍጠር አልሞ ሠርቷል፡፡

የለውጡ መንግሥት ሁሉንም ወገኖች የሚያሳትፍና የሚያግባባ፤ የሚያስተሳስር፣ አብሮነትን በትብብር መንፈስ የሚያጎለብት፤ ብዝኃነትንና አንድነትን የሚያሳልጥ በብሔራዊነት ትርክት ላይ የተመሰረተ ሀገረ መንግሥት እየገነባ መሆኑን ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል፡፡ መንግሥት ያለፉ ቁርሾዎችንና ስብራቶችን የሚጠግን የሽግግር ፍትህ ለመተግበር የሚያስችል ፖሊሲ ለመተግበርም እንቅስቃሴ ላይ መሆኑን፤ ልዩነቶችንና ያላግባቡ ጉዳዮችን በውይይትና በምክክር፤ በሰጥቶ መቀበልና በድርድር ለመፍታት ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን በማቋቋም አስፈላጊወን ሁሉ እያከናወነ እንዳለ ገልጸዋል፡፡

ወርሀ መጋቢት የኢትዮጵያ የመለወጥና የመበልጸግ ፍላጎት እውን የሆነበት ብቻ ሳይሆን ለሁለንተናዊ ብልጽግና፣ ለመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት የተጣለበት ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣበት ጀምሮ የይቅርታና የምህረት እሳቤ በተጨባጭ እንዲተገበር በርካታ ጥረቶች መደረጋቸውን፤ በተቃውሞ ተርታ የነበሩና በፖለቲካ አቋማቸው ምክንያት ለስደት የተዳረጉ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው ሃሳባቸውን በነጻነት እንዲያራምዱ የዴሞክራሲ ምህዳር መከፈቱን፤ እስር ቤት የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ ማህበራዊ አንቂዎችና ታዋቂ ግለሰቦች እንዲፈቱ መደረጉን፤ በእምነት ተቋማት መካከል የነበሩ ችግሮች በምክክር እና በሽምግልና እንዲፈቱ መደረጉንና የዴሞክራሲ ምህዳሩን ያጠበቡ አሳሪ ሕጎች መሻሻላቸውን ተናግረዋል፡፡ እነዚህ ተዳምረው ለአካታች ህብረብሔራዊ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት መሠረት እንዲጣል ረድቷል ነው ያሉት፡፡

ያለፉት ስድስት የለውጥና የብልጽግና ጉዞ ዓመታት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከፍጹም ውድቀትና ስብራት የጠገነ፤ ጣሪያ ነክቶ የነበረውን የውጭ ዕዳ ክምችት ችግርን የታደጉ ውጤታማ የኢኮኖሚ ሪፎርሞች የተከናወኑበት መሆኑንም አንስተዋል፡፡

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሞች የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባልተቋረጠ አግባብ ሁሉንም ውስጣዊና ውጫዊ ተጽዕኖዎች በመቋቋም እድገት እንዲመዘገብ ከማድረጉም በላይ፤ የሀገር ውስጥን ጠቅላላ ምርት በእጥፍ እንዲያድግ አስችሏል፡፡ የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢም እንዲሁ፡፡ በችግር ውስጥ ገብተው የነበሩ እንደ ዓባይ ግድብ ያሉ ትላልቅ ሜጋ ፕሮጀክቶች ከነበሩባቸው ችግሮች ተላቀው ወደ ማጠናቀቂያ ምዕራፍ እንዲሸጋገሩ አድርጓል፡፡

የለውጡ መንግሥት እንደቀደመው ሁሉ የወል አቅሞችን በማጎልበት ቁርጠኛ አቋም አለው በማለት፤ ኅብረ ብሔራዊነትን በማጠናከር ለሁሉም የምትመች ሰላም፣ ፍትህና ርትዕ የሰፈነባት ሀገር ከመገንባት ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ በመገንዘብ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተጀመሩ የለውጥና ሁሉን አቀፍ የሪፎርም ሥራዎችን ከዳር ለማድረስ ርብርቡን አጠናክሮ እንዲቀጥልም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ሚኒስትሩ አክለውም በአማራ ክልል የተጀመረው የሕግ ማስከበር ሥራ ውጤታማነቱን ጠብቆ እንደቀጠለ መሆኑን፤ የሕግ ማስከበር ሥራውን ተከትሎ በተወሰዱ እርምጃዎች ክልሉ ከሞላ ጎደል ወደ ተሟላ ሰላምና መረጋጋት ለመምጣት የሚያስችል ሁኔታ መፈጠሩን፤ የፖለቲካና የአስተዳደር መዋቅሩን የማጥራት፣ መልሶ የማደራጀት አቅሙን የመገንባትና ከየተልዕኮ አኳያ በተቀናጀ መልክ ወደ ተጨባጭ ተግባር እንዲገባ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

የክልሉ ፀጥታ ኃይል ተገቢውን ሥልጠና በመውሰድ ራሱን እንደገና በማደራጀት በየቀበሌውና ወረዳ የአካባቢውን ሰላም በመጠበቅ መረጋጋት እንዲፈጠር አበክሮ እየሠራ መሆኑንም ጠቅሰዋል፡፡

በልዩ ልዩ አሳሳች መረጃዎች ተደናግሮ ከጽንፈኛውና ዘራፊ ኃይል ጎን ተሰልፎ ከነበረው ኃይል ከ12ሺህ በላይ የሚሆኑት የቀረበላቸውን የሰላም ጥሪ ተቀብለው ተሃድሶ በመውሰድ ከኅብረተሰቡ ጋር ተቀላቅለዋል ብለዋል፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች አኩርፈው ተበትነው የነበሩ ከ10ሺህ ያለነሱ የቀድሞ የልዩ ኃይል አባላትም በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት በተሐድሶ ሥልጠናዎች አልፈው ክልሉን ከጥፋት ኃይሎች ለመታደግ የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ እንዳለም ተናግረዋል፡፡

በተደጋጋሚ የተደረገለትን የሰላም ጥሪና ውይይት በረገጠው የሸኔ የሽብር ቡድን ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠሉንም ሚኒስትሩ አንስተዋል፡፡ ባሳለፍነው የመጋቢት ወር የሽብር ቡድኑ በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች ላይ የመከላከያ ሠራዊቱ ባደረገው አሰሳና ዘመቻ መጠነ ሰፊ እርምጃዎችን እንደወሰደ አብራርተዋል፡፡ በርካታ የሽብር ቡድኑ አባላት ከመደምሰሳቸውም በላይ ለዓመታት በብቸኝነት የተቆጣጠሯቸው ዋሻዎች፣ ጫካዎችና እንደ ማደራጃ፣ ማሰልጠኛና የሎጀስቲክ ማከማቻ አድሮ ሲጠቀምባቸው የነበሩ ይዞታዎችን መከላከያ ሠራዊቱ ተቆጣጥሯል ነው ያሉት፡፡ በዚህም ቡድኑ ሲንቀሳቀስባቸው የነበሩ አካባቢዎች የተረጋጋ የሰላም ድባብ እየጎለበተ መምጣቱን ጠቅሰዋል፡፡

በትግራይና አማራ የወሰንና የማንነት ጥያቄ የሚነሳባቸው አካባቢዎች ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ የመከላከያ ሠራዊቱ ሰላምና ደኅንነትን ከአካባቢው ኅብረተሰብ ጋር በትብብር እንደሚቆጣጠርም በመግለጫቸው አንስተዋል፡፡

በተጨማሪም በመጪዎቹ ወራት ሰፋፊ የበጋ ልማት በልዩ ትኩረት እንደሚሰሩ፤ የኑሮ ውድነት ችግር ለመቅረፍ ምርትን በጥራትና በመጠን በማሳደግ የበጋ መስኖን ጨምሮ የሌማት ትሩፋት ላይ እንዲሁ በትኩረት እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡ የኮሪደር ልማት ፕሮጀክትም ከተሞችን ውብና ጽዱ እንዲሁም ለነዋሪዎች ምቹና ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ታልሞ እየተሠራ እንዳለ ጠቁመዋል፡፡

---

## “እንደመንግሥት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የግብር ገቢንም ማሳደግ ይቻላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እንደ መንግሥት በጋራ ጥቅም ላይ በመመስረት በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ ሃሳቦች ወደተግባር እንዲወርዱ የተለያዩ ሥራዎችን አከናውነናል፤ በቀጣይም እናከናውናለን ብለዋል።

በዓለም ላይ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር በላይ ሀብት ያላቸው አንድ ሺህ 200 ስታርት አፖች መኖራቸውን ጠቁመው፤ በአጠቃላይ ሀብታቸው አራት ነጥብ ሦስት ትሪሊዮን መድረሱን ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን አንድ ቢሊዮን ዶላር ሀብት ያለው ስታርት አፕ አለመፈጠሩንና ጉዳዩ በጅማሮ ላይ ያለ መሆኑን አንስተዋል።

ከአምስት ዓመታት በፊት በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረቱ 50 ስታርት አፖች መኖራቸውን አስታውሰው፤ አሁን ላይ ግን 900 መድረሳቸውና ከቁጥር ዕድገቱ ባለፈ በተለያዩ መስኮች ላይ የተሰማሩ መሆናቸው እንደሀገር ተስፋ የሚሰጥ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግሥት በፖሊሲ፣ የቴክኖሎጂ ማዕከላትን በማስፋፋት እንዲሁም ምቹ አሠራርን በማስተዋወቅ ስታርት አፖችን ለማበረታታት ሰፊ ሥራ እያከናወነ መሆኑን የጠቆሙት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የፈጠራ ሥራዎቹ ግን በዋነኛነት በግሉ ዘርፍ እንጂ በመንግሥት የሚከናወኑ ባለመሆናቸው ሁሉም የበኩሉን ጥረት ሊያደርግ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ወጣቶች አዲስ ፈጠራ ሲጀምሩ በቅድሚያ ሥራውን መውደድ፣ ቀጥሎም ሥራውን በራሱ መቻላቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም ፈጠራው ተፈላጊና በገበያ ላይ ሊሸጥ የሚችል መሆኑን ማወቅ አለባቸው ሲሉ አስረድተዋል።

ወጣቶች ትልቅ አስበው ከትንሽ በመነሳት ለሀገር የሚተርፍ የፈጠራ ሥራ ማከናወን እንዲሁም ውስጣቸው ያለውን ችግር ፈቺ የፈጠራ ሃሳብ ወደተግባር በማዋል ገቢ መፍጠር እንዳለባቸው አመላክተዋል።

የስታርታፕ አውዱ ጅማሮ ላይ ቢሆንም ችግሮች ግን የሉበትም ማለት አይደለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኢንተርኔት ዋጋ፣ የቢሮ ኪራይ፣ የኤሌክትሪክ ዋጋው ሲታይ ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ለስታርት አፖች ውድ ቢሆንም በጋራ በመደጋገፍ ስኬታማ መሆን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

ከለውጡ በፊት በቴክኖሎጂ የተደገፈ የፋይናንስ አገልግሎት (ፊንቴክ) የሚያከናውን ካለ በሕግ ደረጃ ወንጀለኛ ሆኖ ተጠያቂ ይሆናል፤ አሁን ላይ ግን በርካታ ተቋማት በዘርፉ ተሰማርተው ገንዘብ እያንቀሳቀሱ ይገኛል ብለዋል። መንግሥት ስታርት አፖችን መደገፍ ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘቡ የተለያዩ ማበረታቻዎችን እያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

በመድረኩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ የሕዝብ ተወካዮችና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤዎች፣ ምክር ቤቱ ክልል ርዕሳነ መስተዳድሮችና የከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች፣ ሚኒስትሮች ሥራ ፈጣሪዎችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

---

## “ክልሎችን በአፈጻጸምና በውጤት ማቀራረብ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

አቶ አደም ፋራህ በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በተካሄደው ድጋፋዊ የመስክ ምልከታ ሪፖርት ውይይት ላይ እንደገለጹት፤ የመስክ ምልከታው በቀጣይ ሊሚከናወኑ ተግባራት ግብዓት የተገኘበት፣ የአመራሩንና የማኅበረሰቡን ችግር የሚፈታ ነው፡፡

የመስክ ምልከታ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የአፈጻጸም ልዩነት እንዳለ የተለየ መሆኑን ገልጸው፤ በግንዛቤ፣ በአፈጻጸምና በውጤት የማቀራረብ ሥራ የቀጣይ ተልዕኮ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን ቅንጅት ለማረጋገጥ እና በሁሉም አካባቢዎች የተቀራረበ አፈጻጸም እንዲኖር የተቀናጀ ሥራ እንደሚሰራ አመልክተው፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከክልል አቻ ተቋማት ጋር እቅድ የማናበብ፣ አፈጻጸምን በጋራ የመገምገምና የተሻለ ተሞክሮን በመቀመር ልምድ እንዲለዋወጡ ይደረጋል ብለዋል፡፡

በመስክ ምልከታው የታዩትን ክፍተቶች ለመፍታት ጥረት መደረጉን ገልጸው፤ በቀጣይም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የተገኘውን ግብዓት የእቅዳቸው አካል በማድረግ ተግባራዊ መፍትሄ የሚሰጡበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሥራ ይከናወናል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ አደም ገለጻ፣ በክልሎች ላለው የአፈጻጸም ልዩነት መሰረታዊ ምክንያቱ የአመራሩ ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት ልዩነት መሆኑን ከመስክ ምልከታው መረዳት ተችሏል፡፡ በአመራሩ ላይ ያለውን የተግባር፣ የቁርጠኝነትና የተነሳሽነት ክፍተት ማጥበብና ማቀራረብ ከተቻለ በሁሉም አካባቢዎች ተመሳሳይ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻል ይሆናል፡፡

የመስክ ምልከታ በተከናወነባቸው አካባቢዎች ኢትዮጵያን ለማበልጸግ በቂ ሀብት ያለ መሆኑን ጠቁመው፤ በየአካባቢው ያለውን ሀብት በአግባቡ አስተባብሮ በመጠቀም፣ የታቀዱ እቅዶችን በህዝብ ንቅናቄ በማስፈጸም፣ በአግባቡ አመራር በመስጠት የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ማድረግ እንደሚቻል አስረድተዋል፡፡

ከሰላም አኳያ ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱ በምልከታው የተረጋገጠ መሆኑን አንስተው፤ በድንበርና በአዋሳኝ አካባቢዎች ላይ የሚነሱ ጥያቄዎችንና ተፈናቃዮችን ወደ ቀያቸው የመመለስ ሥራ ትኩረት የሚሹ ናቸው ብለዋል፡፡

ግብርናን ምርታማነት በማሳደግ ረገድ የግብዓት አቅርቦትና የግይብት ሥርዓቱ በቁልፍ ችግሮች የተነሱ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የገበያ ሥርዓቱን ማሻሻል የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል ከፍተኛ ፋይዳ ያለው በመሆኑ የሚመለከታቸው ተቋማት ተቀናጅተው የግብይት ሰንሰለቱን በማሳጠር አምራችን ሸማችን የማገናኘት ሥራ ሊሠሩ እንደሚገባ አስታውቀዋል፡፡

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ፣ የሌማት ትሩፋት፣ የአረንጓዴ አሻራና ሌሎች ጉዳዮች ላይ አመራሩ በያዘው ልክ ወደ መሬት እየወረዱ ስላልሆነ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራበት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በኮንትሮ ባንድና ማዕድን ላይ አደረጃጀት ቢፈጠረም ለውጥ ማምጣት ስላልተቻለ በቀጣይ በተለየ ሁኔታ ለውጥ የሚያመጣ ሥራን በመሥራት የውጭ ምንዛሬ ገቢን ማሳደግና ኅብረሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ክህሎት መር የሥራ እድል ፈጠራ፣ የትምህርት ጥራትና የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ውስንነት ያለ በመሆኑ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል ነው ያሉት፡፡

በምልከታው የተነሱትን ውስንነቶች የመፍታት፣ በአቅም ግንባታ፣ በቴክኖሎጂ፣ በፖሊሲና በሕግ የመደገፍ ሥራ ከፌዴራል ተቋማት የሚጠበቅ ነው ያሉት አቶ አደም፤ የንቅናቄ ሥራዎች ባለቤት እንዲኖራቸው በማድረግ አፈጻጸሙን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ማቅረብ ይገባል ብለዋል፡፡

የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ በኩላቸው እንደገለጹት፤ ተቋማት በቀጣይነት እንዲሰሩ የተሰጣቸውን ሥራ በቁርጠኝነት ሊሠሩ ይገባል ብለዋል፡፡

ሊያስተምር የሚችልና የሁሉም ክልሎች የተካተተበት የተደራጀ ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የተሞክሮ ልውውጥ የማድረግ እና ምንም ያልሠራ አመራር ካላ የአመራር ለውጥ የማድረግ፣ በፌዴራል ተቋማት የመስክ ምልከታ የማድረግ እና በሚቀጥለው የመስክ ምልከታ ብልሹ አሰራር ያለባቸው ዘርፎች ላይ ትኩረት የማድረግ የቀጣይ ሥራዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

በምልከታው የታዩትን ትኩረትና መፍትሄ የሚሹ ጉዳዮችን ከወረዳ እስከ ፌዴራል ያለው አመራር በአግባቡ ቆጥሮ በመያዝ መሥራት እንደሚገባም አመልክተዋል፡፡

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የመስክ ምልከታ ያቀረቡት የፕላንና ልማት ሚኒስትር ዶክተር ፍጹም አረጋ፤ በሰላም ግንባታ በቀጣይ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮችን መለየታቸውን ገልጸው፤ በወረዳ ደረጃ ኅብረተሰቡ የአካባቢው ሰላምና ፀጥታ ጠባቂና ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፣ በዞንና በክልል ደረጃ በተደጋጋሚ ለፀጥታ መደፍረስ ምክንያት የሚሆኑ አካላትን በማወያየት ሕግ የማስከበር ሥራ በቀጣይ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

ድንበር አካባቢ ያለውን የፀጥታ መደፍረስ በፌዴራል ደረጃ በመፍታት የተጀመሩ የሰላም መሰረተ ልማቶችን በማጠናከር አወንታዊ ሰላም መገንባት እና ከክልል ክልል ያለውን ግንኙነት ማጠናከር እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

አረንጓዴ አሻራን በሚመለከት በ2016/17 ክረምት 208 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ማቀዳቸውን ገልጸው፤ እቅዳቸውን ለማሳካት ሶስት ሺህ 800 የችግኝ ጣቢያዎችን ያዘጋጁ ሲሆን፤ የፍራፍሬ ችግኞች ላይ ትኩረት መደረጉ በጥንካሬ የሚታይ ነው ብለዋል፡፡

ምርትና ምርታማነትን በሚመለከት በኢትዮጵያ ታምርት ሥራ አቁመው የነበሩ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ መመለሳቸው በጥንካሬ የታየ ሲሆን፤ በሌማት ትሩፋት የሚሰሩ ሥራዎች በተበጣጠሰ ሁኔታ መከናወናቸው በውስንነት የታየ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

የአማራ ክልል የመስክ ምልከታ ሪፖርትን ያቀረቡት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ እንደገለጹት፤ የጸጥታ መዋቅሩን መልሶ ከማደራጀት አኳያ ከሕዝቡ ጋር ሰፊ ውይይት በማድረግና የፖለቲካ መዋቅሩን መልሶ የመፈተሽና የማደራጀት ትልቅ ሥራ ተሰርቷል ብለዋል፡፡

ክልሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በልዩ ሁኔታ ለመቅረፍ፣ የሕዝቡን ጥያቄ ለመመለስና አገልግሎቶችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስጠት የተቀናጀ የሰላምና የፀጥታ ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ከምርትና ምርታማነት አኳያ የመብራት መቆራረጥ፣ የፀጥታ መደፍረስ፣ የግብዓትና የፋይናንስ እጥረት በኢንዱስትሪ ልማቶች ላይ እንደ ችግር የተነሳ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአፋር ክልል የመስክ ምልከታን ያቀረቡት የኢንዱስትሪ ሚኒስትር አቶ መላኩ አለበል እንደገለጹት፤ ከሰላም ግንባታ አኳያ በሰሜኑ ጦርነት ከደረሰበት ችግር አገግሞ ፍጹም ሰላም አለባቸው ከሚባሉት አካባቢዎች መካከል አንዱ አፋር ነው፡፡

ምርትና ምርታማነትን በሚመለከት በክልሉ ሰፊ ሊለማ የሚችል መሬት መኖሩን ገልጸው፤ ይህንን ሰፊ መሬት የማልማት ሂደት፣ የእርሻ ሜካናይዜሽን አቅርቦት፣ የግብአት አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች ወደ ሥራ መግባታቸው ነባር ከፍተኛ፣ መካከለኛና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ተስፋ ሰጪ ውጤት ማስገኘታቸው በጥንካሬ የታየ ሲሆን፤ የገበያ ትስስር፣ የመሰረተ ልማት፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና የግብዓት አቅርቦት እጥረት በውስንነት የታዩ መሆናቸውን አስታውቀዋል፡፡

ከሌማት ትሩፋት ጋር ተያይዞ የክልሉን ጸጋ ታሳቢ ያደረገ ሥራ በበቂ ሁኔታ አለመሰራቱ፣ በአንዳንድ ወረዳዎች አለመጀመሩ እና ለሌማት ትሩፋት ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆን በውስንነት የተነሳ ነው ያሉት፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## አዋጁ የአከራይና ተከራይ መብትን ሚዛናዊነት የሚጠብቅ፤ ሕጋዊነትን የሚያጸና ነው!

በተለያዩ ምክንያቶች ከሚደረግ ፍልሰት ጋር በተያያዘ በከተሞች ከፍተኛ የሆነ የመኖሪያ ቤት እጥረት አጋጥሟል። በተለይም አዲስ አበባን ጨምሮ በክልል ዋና ከተሞች ችግሩ ነዋሪዎችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተፈታተነ ይገኛል። ችግሩም በተለይም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ዜጎች “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ችግሩን ለመፍታት በየወቅቱ የተደረጉ ጥረቶች አንድም የችግሩን ስፋት እና ጥልቀት ያገናዘቡ አለመሆናቸው፤ ሁለተኛም፣ በተለያዩ አማራጮች የተደገፉ እና ዘላቂነት ባለው የልማት መስመር አለመጓዛቸው ችግሩ አሁን ላይ ገዝፎ ዜጎችን ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ እያደረጋቸው ይገኛል።

በተለይም በአዲስ አበባ ያለው የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ካለው ፍላጎቶች ጋር አለመጣጣሙ፤ የቤት ኪራይ ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ እንዲንር ከማድረግ ባለፈ፤ ተከራዮች ተከራይተው በሚኖሩት ቤት ውስጥ የሚኖራቸው ቆይታ በደላሎች በጎ ፈቃድና ያልተገባ ተጠቃሚነት ላይ የተመሠረተ እንዲሆን አድርጎታል።

ይህም ተከራዮች እስከ ቤተሰቦቻቸው የተረጋጋ ሕይወት እንዳይመሩ ፈተና ከመሆን ባለፈ፤ በየጊዜው ከሚደረግ የኪራይ ጭማሪ ጋር በተያያዘ ከአቅማቸው በላይ ከገቢያቸው እስከ 70 ከመቶ የሚሆነውን ለቤት ኪራይ በማዋል፤ ለተጨማሪ የሕይወት ፈተና ተጋላጭ እንዲሆኑ፤ ጤናን ጨምሮ ሌሎች መሠረታዊ ፍላጎቶችን በማዛባት ዜጎችን ለተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች እየዳረገ ይገኛል።

ከችግሩ ግዝፈት የተነሳም አብዛኛው የመንግሥት ሠራተኛ እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች ከመሀል ከተሞች እየወጡ ወደ ከተሞች ዳርቻ ለመኖር ተገደዋል። ይህም በራሱ በከተሞች ካለው የትራንስፖርት እጥረት ጋር በተያያዘ ለተጨማሪ እንግልት ዳርጓቸዋል።

ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ፣ የመንግሥትን፣ የነዋሪውንና የባለሀብቶችን ንቁ ተሳትፎ የሚፈልግ ነው። አሁንም ወደ ከተሞች ከሚደረግ ከፍተኛ ፍልሰት ጋር በተያያዘም ልዩ ትኩረት የሚሻ ብቻ ሳይሆን፣ ፈተናነቱንም በቀላሉ የምንሻገረው አይሆንም።

የጀመርነው ልማት በሁለንተናዊ መልኩ እየሰፋ ሲሄድ፣ የመኖሪያ ቤት የመሠረት ልማቶችን በስፋትና በጥራት መገንባት የሚያስችል ሀገራዊ የፋይናንስ አቅም ባለቤቶች ስንሆን ችግሩን ለዘለቄታው ልንሻገረው እንደምንችል ይታመናል። እንደ ሀገር ተስፋ የምናደርገውም ይህንኑ በእጃችን ያለውን መፍትሔ ነው።

እስከዛው ግን ከፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ጋር በተያያዘ ከተፈጠረው ክፍተት ባለፈ፣ በቤት ኪራይ ዙሪያ በደላሎች ያልተገራ ስዕብና በተከራዮች ላይ እየተፈጠረ ያለውን ያልተገባ ችግር ለመቆጣጠር ሕግም የተከተለ የአሠራር ሥርዓት ማስፈን ተገቢ እንደሆነ ይታመናል።

ከዚህ አንጻር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመኖሪያ ቤት ኪራይ ላይ የሚስተዋለውን ኢ-ፍትሐዊ የዋጋ ጭማሪን በመቆጣጠር ጊዜያዊ መፍትሔ ይሰጣል ያለውን የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር አዋጅን ማፅደቁ የሚበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ፤ እንደ አንድ የመፍትሔ መንገድ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

አዋጁ በመኖሪያ ቤት ኪራይ ላይ የሚስተዋለውን የዋጋ አለመረጋጋት በመቆጣጠር በቤት አቅርቦት ላይ የሚስተዋለውን ችግር እንዲረጋጋ የሚያስችል፤ የአከራይና ተከራይ መብትን ሚዛናዊነት የሚጠብቅ፤ ሕጋዊነትን የሚያጸና፣ ግልጸኝነትን የሚያረጋግጥና ሥርዓቱን ከደላሎች ተጽእኖ የሚያላቅቅ እንደሚሆንም ይታመናል።

ከመኖሪያ ቤት ኪራይ ጋር በተያያዘ ለከፋ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የተዳረጉ ዜጎችን፤ በተለይ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ የመንግሥት ሠራተኞች እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች አሁን ላይ ካሉበት የመሳቀቅ ሕይወት በተወሰነ መልኩ በመታደግ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመሩ የሚያስችል ነው።


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኢትዮጵያውያን ፅናትና አንድነት ማሳያ

ክብረአብ

የሕዝብ ቁጥሯ ከ120 ሚሊዮን የተሻገረው ኢትዮጵያ ከድህነትና ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ለመላቀቅ አያሌ ተግባራቶች እያከናወነች ትገኛለች። ከዚህ መካከል የዓባይ ግድብ አንዱ ነው። በተለይ የሀገሪቱ የኃይል አቅርቦት በየዓመቱ በ25 በመቶ አካባቢ እያደገ በመሆኑ ትላልቅ የኃይል ማመንጫዎችን መገንባት ካልቻለች ዕድገቷ ቀጣይነት አይኖረውም።

የዓባይ ግድብ የሀገራችንን የኤሌክትሪክ አቅርቦት ከ70 በመቶ በላይ ከማሳደጉም ባሻገር ግድቡ ሲጠናቀቅ 74 ቢሊዮን ሜትር ኩዩብ ውኃ የሚይዝና 1680 ኪሎ ሜትር ስኩዌር በላይ ስፋት ስለሚኖረው በዚህ ሰፊ ሰው ሠራሽ ሐይቅ ከፍተኛ የሆነ የአሳ ሀብት ማፍራት የሚያስችል ይሆናል። ጥናቶች እንዳመላከቱት በዓይነታቸው ለየት ያሉ ከዘጠኝ በላይ የአሳ ዝርያዎችን ለማርባት በጣም ምቹ እንደሚሆን እና በዓመት ከ10ሺ ቶን በላይ አሳ የማምረት አቅም ይኖረዋል።

> **ከዓድዋ ድል በመቀጠል በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነትና ትብብር የታየበት የዓባይ ግድብ ብዙዎች ፈተናዎችን አልፎ ከመገባደጀው መድረሱ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከተነሱ ሊቋቋማቸው የሚችል ምድራዊ ኃይል እንደሌለ በተግባር ምሳሌ የሆነ ነው ብል ማጋነን አይሆንም**

ግድቡ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ባለፈ በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ሀገራዊ መግባባትን እንዲጎለብት አድርጓል። ግድብ የሁሉን ድጋፍ ያተረፈ ፤ ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ የፖለቲካ አመለካከት፣ የሃይማኖት ልዩነት፣ ሳይገደበው፣ የብሔር፣ የዕድሜ ወይም የጾታ ልዩነት ሳይታይበት በአንድነት ድጋፉን የቸረው ነው።

ሌላው የግድብ ጠቀሜታ በሕዝባችን ውስጥ የቁጠባ ባህልን እንዲዳብር እድል መፍጠሩ ነው። ቁጠባ ለአንድ ሀገር ኢኮኖሚ እድገት አንዱ አመላካች ነው። የዜጎች የመቆጠብ አቅማቸው እያደገ በመጣ ቁጥር የሀገር ውስጥ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ምክንያት ይሆናል።

የዚህ ፕሮጀክት ሌላው ጥቅም የሥራ ዕድል ፈጠራ ነው። ግድቡ ለበርካታ ዜጎቻችን የሥራ ዕድል ይዞ የመጣ ግዙፍ ፕሮጀክት ነው። ከከፍተኛ ባለሙያዎች ጀምሮ እስከ ቀን ሠራተኛ ድረስ በግንባታው ሥራ በመሳተፍ በአጠቃላይ ከ13ሺ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን የሥራ ዕድል ፈጥሯል።

በቀጥታ የሥራ ዕድል ከተፈጠረላቸው ዜጎች ባሻገር እጅግ በርካታ ዜጎች ደግሞ ለእነዚህ ሠራተኞች የተለያዩ አገልግሎቶች በማቅረብ፤ ለአብነት በሸቀጣሸቀጥ፣ ምግብ፣ ትራንስፖርት በማቅረብ ተጠቃሚ ሆነዋል።

በተጨማሪም በዓባይ ግድብ ሳቢያ በበርካታ አካባቢዎች ህብረተሰቡ ለአካባቢ ጥበቃ ሥራ እንዲነሳሳ ምክንያት ሆኗል። ህብረተሰቡ የግድቡ ዕድሜ እንዲጨምር በየአካባቢው የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን በተለይ በችግኝ ተከላና አፈር ጥበቃ ሥራዎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ እየተረባረበ ይገኛል።

ሌላው የግድቡ ጠቀሜታ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል በተፋሰሱ ሀገራት መካከል እንዲነግስ በማድረጉ ከሀገራት ጋር አዲስ የመተማመንና የመተባበር ዲፕሎማሲን እንዲፈጠር አስችሏል። የግድቡ መጀመር ለእኛ ኢትዮጵያን ፍትሃዊ አመለካከታችንን ለዓለም ለማሳወቅ ጥሩ አጋጣሚን ፈጥሮልናል።

ኢትዮጵያ ምን ያህል ፍትሃዊ እንደሆነች የዓለም ሕዝቦች የተረዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የሀገራችንንም የመደራደር አቅም አሳድጓል። የሀገራችንን ገጽታም እጅጉን ቀይሮታል። የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በተለይ ግብጻዊያንን ለውይይት እና ምክክር በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲቀመጡም አድርጓል።

ከተጀመረ 13ኛ ዓመቱን ያስቆጠረው የዓባይ ግድብ፣ በኢትዮጵያውያን የፋይናንስና የሞራል ድጋፍ ከተገነቡ ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች የመጀመሪያው ተደርጎ ይጠቀሳል፡፡ በተለይም የግድቡ ግንባታ ከጅምር እስከ አሁን ውጫዊና ውስጣዊ ፈተናዎች ባሉበት ሁኔታ አልፎ በመገባደድ ላይ መሆኑም ኢትዮጵያ በፅናት እየተሻገረች ስለመሆኗ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በተለይም በዓባይ ተፋሰስ ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ ውሃውን ለብቻችን እንጠቀም የሚሉ ሀገራት ኢትዮጵያን ያላሳተፉ የቅኝ ግዛት ውሎች ዳግም ለማጽናት የዓረብ ሊግን በመጠቀም ዘመቻዎች ሲደረጉ ቢቆዩም የኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ ቁርጠኝነት፣ ብርቱ የዲፕሎማሲ ጥረትና የማህበረሰብ ተሳትፎ ተደምረው ጫናዎችን በማለፍ ግድቡ አሁን የደረሰበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ አስችለዋል።

ኢትዮጵያ በ2003 ዓ.ም ላይ የዓባይ ግድብን መገንባት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ግብፅና ሱዳን ተቃውሞና ስጋታቸውን በተለያዩ መንገዶች ሲገልጹ እስከ ዛሬ ይደመጣሉ። ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን ላለፉት አሥር ዓመታት በዓባይ ወንዝ ጉዳይ ከስምምነት ለመድረስ ሲደራደሩ የነበረ ቢሆንም፤ እስካሁን ሦስቱንም ሀገራት የሚያስማማ ሁሉን አቀፍ መግባባት ላይ መድረስ አልተቻለም።

እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ የአንዳንድ የታችኛው ተፋሰስ ሀገራት ሴራና ተንኮል ነው። በእኔ እምነት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም በተቃራኒ የሚቆሙ እነዚህ ሀገራት የዓባይ ግድብ የቅርብ ጊዜ ምክንያት ሆናቸው እንጂ በታሪክ አጋጣሚ ሁሉ የኢትዮጵያን ዕድገት የማይፈልጉና እንደ ስጋት የሚመለከቱ ሀገራት ናቸው።

ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢ የሕዝብ ብዛት ያላት ግብፅ፤ ከኢትዮጵያ 15 እጥፍ የሚያህል የኃይል ፍጆታ አላት። የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ፍጆታ 10.7 ቢሊዮን ኪሎዋት ሲሆን የግብፅ ደግሞ 159 ቢሊዮን ኪሎዋት ነው። ይህ እውነት የሚያሳየን የግብፅ አካሄድ ከመጠን ባለፈ በእራስ ወዳድነት የተሞላና የኢትዮጵያን ዕድገት እንደ ስጋት የማየት በሽታ የተጠናወታት መሆኑን ነው።

ከዓድዋ ድል በመቀጠል በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነትና ትብብር የታየበት የዓባይ ግድብ ብዙዎች ፈተናዎችን አልፎ ከመገባደጀው መድረሱ ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከተነሱ ሊቋቋማቸው የሚችል ምድራዊ ኃይል እንደሌለ በተግባር ምሳሌ የሆነ ነው ብል ማጋነን አይሆንም።

በአጠቃላይ የዓባይ ግድብ በሀገሪቱ እየጎለበተ ላለው ጠንካራ ህብረ-ብሔራዊ አንድነት አንድ ማሳያ ከመሆኑም ባሻገር ለሀገራችን የገጽታ ግንባታ እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ይህ ፕሮጀክት በሀገራችን ሕዝቦች መካከል የይቻላል መንፈስ እንዲፈጠር ሲያደርግ ለሌሎች ታዳጊ ሀገራት ደግሞ በተፈጥሮ ሀብታቸው እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ መንገድን አመላክቷል።

የኢትዮጵያ ሕዝባች ፍትሃዊነት ለዓለም ያሳወቁበት አንዱ ማሳያ ነው። የተፋሰሱ ሀገራትም የጋራ ሀብታቸውን በትብብር እና በመደጋገፍ ከመጠቀም ውጭ ሌላ አማራጭ እንደማይኖራቸው የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በተጨባጭ አሳይተዋል።

የዓባይ ግድብ የትላንት አባቶቻችን የሠሩት የዓድዋ ገድል የዛሬ ትውልድ ኩራት እንደሆነው ሁሉ የዚህ ትውልድ ዓድዋ ደግሞ ከድህነት ጋር ተፋልሞ ድል በማድረግ የሚገኝ በመሆኑ ሁሉም ዜጋ የራሱን ዓድዋ ለመሥራትና ለልጆቹ በጀግንነት የሚናገረው ታሪክ ለማኖር አቅሙ በፈቀደው ሁሉ መረባረብ አለበት እላለሁ። ሰላም!

# የቤኒሻንጉል ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሠራርን መሠረት ያደረገው የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽ

ዳግም ከበደ

የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል የበርካታ ባህል፣ ታሪክና የተፈጥሮ ሀብቶች መገኛ ነው። ክልሉ የልዩ ልዩ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች መኖሪያም ሲሆን፣ በመቻቻልና በፍቅር የሚኖርበት የኢትዮጵያ ክፍል ነው።

ክልሉ ከሚታወቅባቸው ባሕላዊና ታሪካዊ እሴቶቹ መካከል የቤኒሻንጉል ብሔረሰብ ባሕላዊ ቤት አሠራር ይጠቀሳል፤ በዚህ የቤት አሠራር ላይ ተመስርቶ የተገነባው ጥንታዊው የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽም ሌላው የክልሉ ታሪካዊ ቅርስ ነው። የሼህ ሆጀሌ ችሎት አዳራሽ እና የቤኒሻንጉል ባሕላዊ ቤት አሠራር በኢትዮጵያ የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ተመዝግበዋል።

የክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቋንቋና የጋራ ባህል እሴቶች ዳይሬክቶሬት የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽ ታሪክ ከ1817 እስከ 1931 በሚል ያዘጋጀው ጥናታዊ ጽሑፍ አዘጋጅ አቶ ፈንታሁን ደጀን እንደገለጹት፤ የሼህ ሆጀሌ ችሎት አዳራሽ በአሶሳ ወረዳ በዓይነቱ የመጀመሪያ ከመሆኑ ባሻገር በወቅቱ የአሶሳ አስተዳደር ማዕከላዊ መቀመጫ በመሆን አገልግሏል። ሼህ ሆጀሌም ይህን ማዕከል ከማስገንባት ባለፈ በመሪነት ዘመናቸው ከዚሁ ማዕከል በመነሳት ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ተግባራትን በማከናወን የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱበት ነው።

የአካባቢውን ተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም የችሎት አዳራሹን ከተለመደው የወቅቱ የቤት አሠራር በማሻሻል በጡብ ማስገንባታቸው ችሎት አዳራሹ ረጅም እድሜ የቆየና በግዘፈ አካል እንዲገኝ ማስቻሉም ይጠቅሳሉ። በተለይ ፍትህ ለጎደላቸው፣ ለተጣሉ፣ ፍርድ ለሚያስፈልጋቸው ሁሉ በዚህ አዳራሽ ውስጥ አባቶችንና ባለሚሎቻቸውን ጭምር በማሳተፍ ማህበረሰቡን በቅንነት ያገለግሉበት እንደነበር ይገልጻሉ።

## የክብ ቅርፅ ቤት

የጥናቱ አዘጋጅ አቶ ፈንታሁን፤ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በተለይም በቤኒሻንጉል ብሔረሰብ ዘንድ የክብ ቅርፅ ባህላዊ የቤት አሠራር ዘይቤ የተለመደ መሆኑን ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ አብዛኞዎቹ ብሔረሰቦች ክብ ቅርፅ ያላቸው ቤቶች እንደሚሰሩ በመጥቀስም፤ ክብ ቤት መሥራት ሰዎች ከተግባራዊ ልምዶቻቸውና ከአካባቢ ሁኔታቸው ያገኙትን ዕውቀት በመጠቀም የመረጡት መሆኑን ያብራራሉ። በክብ ቅርፅ የሚሠራ ቤት የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የሚገልጹት የጥናቱ አዘጋጅ፤ ክብ ቤት የተሻለ ጥንካሬ ያለው መሆኑ፤ ከጉልበትና ቁሳቁስ አንፃር በተነፃፃሪነት ወጪው ቀላል እንዲሁም ውስብስብነት የሌለውም መሆኑ ከጥቅሞቹ ጥቂቱ እንደሆኑ ይገልፃሉ። በውስጥና በውጭ ተጨማሪ ቅጥያዎችን ለመሥራት ምቹ መሆኑንም ነው የጠቆሙት።

አቶ ፈንታሁን እንዳብራሩት፤ የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽ የቤኒሻንጉል ባህላዊ ቤት ሥራርን የተከተለ ነው። በአሶሳ ወረዳ ቤኒሻንጉል የሚታየው ባህላዊ የቤት አሠራር በቅርጽ ክብ ሆኖ ለግንባታውም ጥቅም ላይ የሚውሉት ቁሳቁስ እንጨት፣ ቀርከሃ፣ ሣርና ለመምረጊያ አፈር ናቸው። የቀርከሃ ተክል በዋነኛነት ለቤት መሥሪያነት ይውላል።

የሼህ ሆጀሌ አዳራሽ ግን በወቅቱ ለዘመናዊ ቤት አሠራር ጥቅም ላይ ከሚውለው ጡብ የተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ ቅርጹና የባህላዊ ቤት አሠራር ሥርዓቱ የማህበረሰቡን ባሕልና ዘይቤ እንዲወክል ተደርጎ የታነፀ መሆኑን ተናግረዋል።

በብሔረሰቡ ዘንድ ‹‹እያንዳንዱ አባወራ የቤተሰብ መኖሪያና ሌላ ተጨማሪ የእንግዳ ማረፊያ “ህልዋ” ይሰራል›› የሚሉት አቶ ፈንታሁን፤ ከመንደሩ /ከሰፈሩ/ ከሚኖሩ ታዋቂ ሰዎች ግቢ ከዋናው ቤት በተጨማሪ “ዴዋን” የተባለ ለመመካከሪያ፣ ለመሰባሰቢያና ለእርቅ መፈጸሚያ እንዲሁም ለእንግዳ መቀበያ ሆኖ የሚያገለግል ሰፊ ቤትም እንደሚሠራ አብራርተዋል። የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽም ያንን መሠረት አድርጎ ማህበረሰቡን ለማገልገል ታሳቢ በማድረግ እንደተሠራ ተናግሯል።



የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽ

## ባሕላዊ የቤት አሠራር ቅደም ተከተል

አቶ ፈንታሁን እንዳብራሩት፤ ባሕላዊ ቤቱ ከመሠራቱ አስቀድሞ የሚያርፍበት ቦታ በሚገባ እንዲፀዳ ይደረጋል። በመቀጠል ለእንጨት ወይም ቀርከሃ ማቆሚያ ጉድጓድ ወደ ታች በክብ መስመር ወይም ምልክት በተደረገበት ልክ ይቆፈራል። በአብዛኛው ቋሚዎቹ ባለ ያላቸው እንጨቶች ናቸው። የጉድጓዱ ስፋትና ጥልቀት መጠን እንደ ቋሚው እንጨት ወይም ቀርከሃነትና እንደ ቤቱ ትልቅነት ደረጃ ተገምቶ የሚዘጋጅ ነው።

ቤቱ የሚያርፍበት ወለል የሚለካው በእንጨት ወይም በክንድ በተለካ ገመድ ነው። ቋሚ እንጨቶቹ ወይም ቀርከሃዎቹ ከተተከሉ በኋላ የተሰነጠቀ ቀርከሃ በተተከሉት እንጨቶች ከአንዱ በር ተነስቶ ወደ ጎን በተተከሉት ቋሚዎች እየተጠላለፈ (ከቋሚዎቹ ከአንዱ በውስጥ አቅጣጫ ከቀጣዩ ቋሚ ደግሞ ከውጭ አቅጣጫ በውስጥና በውጭ እያቀያየሩ) በማሳለፍ ከወለሉ ጀምሮ እስከ ግድግዳው አናት ድረስ በዙር እንዲቀጥል ይደረጋል። የግድግዳ ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ተሰንጥቆና ተደራርቦ በጥቅል መልክ የተዘጋጀ ቀርከሃ በክቡ የግድግዳ አናት ቋሚ ባላዎች ራስ ላይ ዙሪያውን እንዲያርፍ ተደርጎ ልክ እንደ “ቢም” ይቀመጣል።

‹‹የግድግዳ ሥራው እንደተጠናቀቀ የጣራ ሥራው ይቀጥላል›› የሚሉት አቶ ፈንታሁን፤ የጣራ ሥራው በቀርከሃ ወራጅ ከግድግዳው ድምድማት ወይም ራስ ጀምሮ ዙሪያን ወደ ላይ ከቤቱ መካከለኛ ምሰሶ ጫፍ እንዲገጥም ተደርጎ እንደሚታሰር ይገልፃሉ። ቀጥሎም በጣሪያው ዙሪያ ወደ ጐን የተሰነጠቀ ቀርከሃ ከወራጅ ቀርከሃው ጋር እየታሰረ በተወሰነ ርቀት ዙሮ ገጠም ማገር ተሰርቶ ይጠናቀቃል ሲሉ ያብራራሉ። በመጨረሻም ጣራው በሳር እንዲሸፈን ተደርጎ ግድግዳው ከአፈር በተዘጋጀ ጭቃ ይመረጋል ይላሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የቤቱ ውስጣዊ የመሀል ዙሪያ አለፍ አለፍ ብሎ በክብ በሚተከሉ ቋሚ ወጋግራዎች ወይም ያለ ምንም ምሰሶ እንደ ቤቱ ትልቅነትና መጠን ታይቶ ይሰራል። የትላልቅ ቤቶች በረንዳው ሰፊ ሲሆን የጣራው ጫፍ ወደ መሬት አቅጣጫ ከሰው ቁመት ዝቅ ብሎ ይወርዳል። በረንዳውም በዙሪያው የእንጨት ቋሚዎች ወይም እንደ “ኮለን” የሚያገለግሉ ድጋፎች ይሰራለታል።

‹‹የቤኒሻንጉል ባሕላዊ ቤት አሠራር ዋነኛ ግብዓት የቀርከሃ ተክል ነው፤ የዚህ መነሻ ምክንያት በአካባቢው የቀርከሃ ተክል በቅርበትና በብዛት መገኘት ነው›› የሚሉት አቶ ፈንታሁን፤ ቀርከሃ ለክብ ቤት ሥራ የተመቸ መሆኑም ሌላው ምክንያት መሆኑን ያብራራሉ። ቀርከሃ በቤት ግንባታው ሂደት ከግድግዳ እስከ ጣራና የሣር ክዳን ድረስ አገልግሎት መስጠት መቻሉና፤ ለአዘጋጃጀት ለማጓጓዝና ለሥራ ያለው ቅለትም በማህበረሰቡ ተመራጭ የመሥሪያ ግብዓት እንዳደረገው አስታውቀዋል።

## ሼህ የሆጀሌ ችሎት አዳራሽ መነሻ

ሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሹን ያሰሩት “አጉመላ” በተባለ ቦታ መሆኑን አቶ ፈንታሁን ይናገራሉ። “አጉመላ” ትርጉሙ “አጥር ውስጥ” “ግቢ ውስጥ” ማለት መሆኑንም ይገልፃሉ። በ“አጉመላ”በክብ ዙሪያ የተተከሉ ዛፎች መኖራቸውንም ያነሳሉ።

ከላይ በዝርዝር ለማንሳት እንደተሞከረው የቤንሻንጉል ብሔረሰብ ባሕላዊ የቤት አሠራር ዙሪያው ክብ ነው፤ ጣሪያው ደግሞ ሾጠጥ ያለ ነው። የቤቱ አካል የተዋቀረው ከቀርከሃና እንጨት ሲሆን፣ የቤቱ ዙሪያ በረንዳና የውስጡ ማዕከላዊ ክፍል ዙሪያውን የሚተከሉ ባለ “ባላ” እንጨቶች ወይም ደጋፊዎች ያሉት ነው።

የሼህ ሆጀሌ የችሎት አዳራሽ ይህን የቤኒሻንጉል ብሔረሰብን ባህላዊ ቤት አሠራር መሠረት በማድረግ በሥፍራው መታነጹን አቶ ፈንታሁን ጠቅሰው፤ የማህበረሰቡን ባህል፣ ማህበራዊ መስተጋብር እንዲሁም ወግና ልማድ እንዲያንፀባርቅና እንዲወክል ተደርጎ በአስተዳዳሪው መሠራቱን ይገልፃሉ።

በእያንዳንዱ አባወራ ወይም ቤተሰብ መኖሪያ ከዋናው ቤት በተጨማሪ አንድ የእንግዳ ማረፊያ ቤት እንደሚኖር በመጠቅስም ዋናው ቤት ቁሳቁስ፣ እህል፣ የምግብ ዝግጅት ማድረጊያና በአጠቃላይ ለቤተሰቡ መኖሪያነት እንደሚያገለግል ይናገራሉ። ከዋናው ቤት በተጨማሪ የሚሠራው ሁለተኛው ቤት “ህልዋ” ወይም “አልህልዋ” ተብሎ እንደሚጠራ ጠቅሰው፣ አገልግሎቱ እንግዳ የሚያርፍበት፣ አባወራ ከጎረቤት ጋር የሚጫወትበት፣ ከእንግዶች ጋር አብሮ የሚመገብበትና ቡና የሚጠጣበት፣ ምክክር የሚያደረግበት፤ በተለይም የአባዎራዎች ማህበራዊ ግንኙነት መድረክ መሆኑን ያስረዳሉ።

ከዚህ ሌላ በአንድ ሰፈር ወይም ጎረቤቶች ታዋቂ ከሆነ ትልቅ ሰው ግቢ ውስጥ ከመኖሪያው በተጨማሪ “ዴዋን” ተብሎ የሚጠራ ቤት ይሠራል። ይህ ቤት የአካባቢው ሰዎች የሚሰበሰቡበት፣ የሚወያዩበት አብረው የሚበሉበትና የሚጠጡበት፣ የሚመክሩበት እርቅ የሚፈጽሙበት፣ በጋራ የሚወስኑበት ማዕከል ነው። የችሎት አዳራሹም የማህበረሰቡን እነዚህን ሁሉ እሴቶች እንዲያቅፍ መደረጉን አቶ ፈንታሁን ይገልፃሉ።

‹‹የሼህ ሆጀሌ ችሎት አዳራሽም በቅርፅ ክብ ሆኖ ዙሪያውን የበረንዳ ቋሚዎች ያሉትና ጣራው በቀርከሃና በእንጨት የተሠራ ከፍ ያለና የአካባቢውን ባህላዊ ቤት አሠራር የተከተለ ነው›› የሚሉት አቶ ፈንታሁን፤ አገልግሎቱም ልክ እንደ ገፅታው ሁሉ በ“ህልዋ”ና ይበልጡንም በ“ዴዋን” ከሚሰጡ አገልግሎቶች ጋር የተያያዘ መሠረት ያለው መሆኑን ያስረዳሉ።

የሼህ ሆጀሌ አልህሰን ችሎት አዳራሽ እነዚህን አካባቢያዊ ገፅታዎችና ክንዋኔዎች ወደ ተሻለ ደረጃ በማሳደግ የተገነባ የአስተዳደርና ፍትህ መስጫ አዳራሽ መሆኑንም አስታወቆ፣ የአካባቢውን ጥሬ ሀብት በመጠቀምና በሰው ጉልበት መሠራቱ ሌላው ከባሕላዊ መሠረቱ የሚያመሳስለው መሆኑንም ያብራራሉ።

## የችሎት አዳራሹ አገልግሎት

አቶ ፈንታሁን እንደሚሉት፤ የችሎት አዳራሹ የተለያዩ ግልጋሎቶችን ይሰጥ ነበር። በተለይ የአስተዳደርና የፍትህ አገልግሎት በመስጠት ይታወቃል። ሼህ ሆጀሌ ከአንድ በላይ ሚስቶች ስለነበራቸው በየሚስቶቻቸው እየተዘዋወሩ ይኖሩ እንደነበር የሚጠቅሱት የጥናቱ አዘጋጅ፤ በሚዘዋወሩባቸው የግዛት ክልሎች ለሚቀርቡላቸው አቤቱታዎችና ጉዳዮች ወዲያው መፍትሔ ሰጥተው ይመለሱ እንደነበር የተገኙ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩ ይገልፃሉ። በሌላ በኩል በመቀመጫቸው አሶሳ በችሎት አዳራሹ ቀርበው ከሚታዩ ጉዳዮች መካከል የግል ጉዳዮች፣ የባልና ሚስት፣ ከብድር አመላለስ ጋር የተያያዘ ጠብና አልፎ አልፎ ከባለቤትነት /ይገባኛል ባይነት/ ጋር የተገናኙ ክርክሮች ዋና ዋናዎቹ እንደነበሩ ይናገራሉ።

እነዚህን ችግሮች ባለጉዳዮች እንዳመለከቱ እንደነገሩ ቅለትና ክብደት እየታየ ራሳቸው ሼህ ሆጀሌ ቀጥተኛ ውሳኔ ሰጥተው ይመልሷቸው እንደነበርም አመልክተው፣ ጠንከር ያሉ ጉዳዮችና ችግሮች ሲያጋጥሙ በታዋቂ ሰዎች ማለትም የሀገር ሽማግሌዎችንና የሃይማኖት አባቶችን በማማከር የመፍትሔ ሃሳብ አቅርበው በይበልጥ በስምምነት ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጉ እንደነበርም አቶ ፋንታሁን አስታውሰዋል።

ይህ በቡድን ተወያይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት አሠራር “ሹራ” ተብሎ እንደሚጠራም ይገልፃሉ። ለሼህ ሆጀሌም ሆነ በአጠቃላይ “ሹራ” ለተባለው አማካሪ ቡድን የሚቀርቡ ጉዳዮች በተጎጂ ግለሰቦች፤ ቅሬታ በተሰማቸው ሰዎችና፤ በተዋረድ በሚገኙ “መከ” “ሙቀደም” “ሸህ” ተብለው በሚጠሩ የአካባቢው አስተዳዳሪዎች ሊፈቱ ያልቻሉ ግጭቶችና በእነሱ አመልካችነትም ጭምር የሚቀርቡ ጉዳዮች መሆናቸውን አቶ ፈንታሁን ከዝግጅት ክፍላችን ጋር በነበራቸው ቆይታ አብራርተውልናል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# በወታደራዊ የቴክኖሎጂ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደረገው ወጣት

**ክብረአብ በላቸው**

በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂና በአዲስ የፈጠራ ሥራ መታገዝ ግድ ሆኗል። ያለ ቴክኖሎጂ ያለሙበት መድረስ ከባድ እየሆነ መጥቷል። ከእነዚህ ዘመን አፈራሽ የቴክኖሎጂ ዘርፎች መካከል አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ወይም የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቀዳሚውን ስፍራ እየያዘ መጥቷል።

ያደጉትም ሆኑ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ቴክኖሎጂው በሚያስፈልጋቸው ዘርፎች እንደየሁኔታው እየተጠቀሙበት ችግሮቻቸውን እየፈቱ ይገኛሉ። ኢትዮጵያም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ትገኛለች። የሰው ሠራሽ አስተውሎት ቴክኖሎጂን በመጠቀም የግብርና፣ የጤና፣ የደህንነት እና መሰል ዘርፎችን አቅም ለማሳደግ እየተሠራ ነው።

ወጣት ሳሙኤል ዘካሪያስ ይባላል። ውልደትና እድገቱ በአሁኑ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ ዞን ነው። የ12ኛ ክፍል ተማሪ የሆነው ሳሙኤል ከልጅነቱ ጀምሮ ለቴክኖሎጂና ለፈጠራ ሥራ ልዩ ተሰጥኦ አለው። ከአካባቢው ከሚያገኛቸው የወዳደቁ ነገሮች የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን መሥራት የጀመረው ገና በልጅነቱ ነበር። ወደ ፈጠራ ሥራ እንዲገባ ምክንያት የሆነው ነገሮች እንዴት እንደሚሠሩ ለማወቅ ባለው ከፍተኛ ጉጉት እንደሆነ የሚናገረው ሳሙኤል፤ በአንድ ወቅት በትውልድ አካባቢያቸው በመንገድ ግንባታ ሥራ የተሰመሩ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚሰሩትን ሲመለከት ስለቴክኖሎጂ ደጋግሞ በማሰብ ጉዳዩ ውስጡ እንደሰረፀ ይናገራል።

በወቅቱ የውጭ ሀገር ዜጎች የሚሰሩትን "በየቀኑ እየሄድኩ እመለከት ነበር" የሚለው ሳሙኤል፤ ነገር ግን ከባለሙያዎቹ መካከል አንድ ቻይናዊ ማሽኖችን በምን መልኩ እንደሚጠቀሙ ከሌሎች የዕድሜ እኩዮቹ በተለየ መልኩ በትኩረት ስለሚከታተል ለእርሱ ጥሩ አመለካከት እንዳልነበረው እና እንደማይወደው ያስታውሳል።

አንድ ቀን ይህ ቻይናዊ የኮንስትራክሽን ማሽኑን ሞተር ሳያጠፋ አቁሞ ከእንግዶች ጋር እያወራ በነበረበት ወቅት፤ ሳሙኤል ማሽኑን ለማሽከርከር ወጣ። በዚህ ምክንያት ደግሞ ወደዚያ አካባቢ እንዳይቀርብ በመከልከሉ «ማሽኑ እራሴ ለምን አልሰራውም።» በሚል ተነሳሽነት ወደ ፈጠራ ሥራ እንደገባ ያስረዳል።

በመጀመሪያ የፈጠራ ሥራው አነስተኛ አፈር ማንሻ ኤክስካቫተር የሠራው ሳሙኤል፤ በመቀጠልም በጤና፣ በግብርና እና በወታደራዊ ቁሳቁሶች ላይ ትኩረቱን በማድረግ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ችሏል። በዋናነት የፈጠራ ሥራዎቹ ለወታደራዊ አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎችን ማምረት ላይ እንደሚያተኩር የሚናገረው ሳሙኤል፤ የእዚህ ምክንያትም ሀገሩ ኢትዮጵያ በማንም የማትዳፈር ኃያል ሀገረ ሆነ መቀጠልን ህልሙ መሆኑን ያስረዳል።

የ11ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት #ETR S1KM የተባለ ሮኬት የሠራው ሳሙኤል፤ አንድ ኪሎ ሜትር ድረስ የመወንጨፍ አቅም ያለው መሆኑንና፤ ሮኬቱን የሚሸከም መኪና አብረው መሥራቱን ይናገራል። በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት የገንዘብ ድጋፍና ትብብር የተሰራችው ሮኬት በተሳካ መልኩ ሙከራ ተደርጎባት እንደነበር ይናገራል።

ይህንን ሥራ ለመሥራት በተጨማሪነት ምን እንዳነሳሳው ወጣቱ ሲናገር፤ ኢትዮጵያ ከሸማችነት ወደ አምራችነት በምታደርገው ጉዞ ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዳለበት ያምናል። በዋነኝነት ደግሞ ኢትዮጵያ ከላት አነስተኛ የውጭ ምንዛሬ አንፃር ለወታደራዊ መሳሪያ ግዥ የምታወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረት በማለም እንደሆነ ይገልፃል።

ሌላኛው ጉዳይ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል ለማፍራትና የሥራ ዕድል እንዲያገኝ በማሰብ ወደዚህ ሥራ እንደገባ የሚገልጸው ወጣት ሳሙኤል፤ ገና ከጅምር




ባለው ሥራ ለነገ ትልቅ ህልም በማለም ሥራውን አጠናክሮ ስለመቀጠሉ ይናገራል።

ለሀገር ደህንነት ከምንም ነገር በላይ ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ነው የሚለው ወጣቱ፤ ኢትዮጵያ ብዙ ዓይነት የጦር መሳሪያዎችን ከራሺያ፣ ከቱርክ፣ ከቻይና፣ ከአሜሪካ፤ ከእስራኤል በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ወደ ሀገር ውስጥ የምታስገባ መሆኑን በማስታወስ፤ ስለዚህ ይህንን የውጭ ምንዛሬ ለማስቀረት ከፍ ሲልም በረዥም ጊዜ ሂደት የጦር መሳሪያ ወደ ወጭ ለመላክ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎችን ለማሳደግ፤ እንዲሁም የሀገር ደህንነትን በራስ አቅም ለማስጠበቅ ትልቅ ህልም ይዞ የምርምር ሥራዎቹን እንደሚሰራ ይናገራል።

የመጀመሪያ ፕሮጀክቶቹን የሠራቸው ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ሲሆን፤ የወላይታ ዞን አስተዳደር ድጋፍና ክትትል በማድረግ ለተሠሩ ሥራዎችም የምስክር ወረቀቶች የድጋፍ ደብዳቤ የተሰጠው መሆኑ ይበልጥ እንዳበረታታው ተናግሯል። ጉዳዩ የሚመለከታቸው የወላይታ ዩኒቨርሲቲ፣ የዞኑና የክልሉ መንግሥት ለሥራው አጋርነት በማሳየት እንደደገፉት እና ይህ ድጋፋቸውም ለውጤታማነቱ ትልቅ ሚና እንደነበርው ያስረዳል።

በቅርቡ ኢትዮጵያ BM 21 የተሰኘ አዲስ ሮኬት የሠራው ወጣት ሳሙኤል፤ ስለዚህ ሥራው ሲናገር፤ ከስድስት እስከ አስር ኪሎ ሜትር ማስወንጨፍ የሚችል የራሱ ማዘዣ ሲስተም ቦርድ ያለው 330 ዲግሪ እየዞረ የተሰጠውን ተልዕኮ መወጣት የሚችል በሰው ሠራሽ አስተውሎት የሚታገዝ አስተማማኝነቱ የማያጠራጥር እንደሆነ ይናገራል።

በቅርቡ በሠራው ሥራ ደግሞ በወላይታ ሶዶ ከተማ የሚገኙ ሞህበና ቻይና ጋራዥ የተሰኙ የግል ድርጅቶች ከፍተኛ ድጋፍ እንዳደረጉለት ይናገራል። ሃሳብ ያለው ሰው ያንን ወደ ተግባር ለመለወጥ ሲያስብ በሃሳብ፣ በገንዘብ ከጎን የሚቆሙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች መኖር ወሳኝ ነው የሚለው ሳሙኤል፤ ለእሱም ውጤታማነት የእነዚህ ግለሰቦች ድጋፍ ትልቅ ብርታት እንደሆነው ያስረዳል።

ከሮቦቲክስ፣ ከኮዲንግ እንዲሁም ከሰው ሠራሽ አስተውሎት ጋር በተገናኘ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ በሚገኘው በኢትዮጵያ መረጃ መረብ ደህንነት፤ በሮቦቲክስና በኢንዱስትሪያል አውቶሜሽን በኤይሮ ስፔስ ዘርፍ ተሳትፎ እያደረገ የሚገኘው ወጣት ሳሙኤል፤ በተቋሙ የተለያዩ ሥራዎች እየሠረ ቆይቷል።

ከተቋሙ ጋር አሁንም በአጋርነት እየሠራ እንደሆነ የሚገልጸው ሳሙኤል፤ የተለያዩ ስልጠናዎችን እየወሰደ እንደሆነ እና እያከናወነ ለሚገኘው የፈጠራ ሥራም የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ድጋፍ እንዳገኘ እንዲሁም ተቋሙ ሁልጊዜም ከጎኑ የማይለይ በመሆኑ ለተቋሙ አመራሮች ያለው ምስጋና የላቀ እንደሆነ

> **"ሁልጊዜ ችግሮች መልካም አጋጣሚ ይዘው ይመጣሉ ብዬ አምናለሁ" የሚለው ሳሙኤል፤ ሰው የራሱን አስተያየት ይሰጣል፤ መርጦ መውሰድ ደግሞ የግለሰቡ ኃላፊነት ነው**

ይገልጻል።

ስለሚሰራቸው ወታደራዊ ምርቶቹ አጠቃላይ እውነታ ወጣት ሳሙኤል ሲናገር፤ የወታደራዊ ቁሶቹ ከሰው ሠራሽ አስተውሎት ጋር የተገናኙ፣ የወደፊት ጥቅማቸው እጅግ የላቀ የሰው ልጅ መወጣት የማይችላቸውን ሥራዎች መሥራት የሚችሉ ዓለም እየሄደበት ባለው የቴክኖሎጂ ልቀት የሚሰሩ በመሆኑ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ በሁሉም ዘርፍ ጥቅሟን ማስጠበቅ እንድትችል አቅም የሚሆናት እንደሆነ ይናገራል።

ወጣት ሳሙኤል፤ እነዚህ በራስ አቅም የሚሰሩ ሥራዎች ለሀገር ያላቸው ጠቀሜታ ላቅ ያለ በመሆኑ የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅቶች ቴክኖሎጂን መሠራት አድርገው ለሚነሱ ወጣቶች በሁሉም አቅጣጫ ድጋፍ በማድረግ ሀገሪቱ ከድህነት ለመውጣት የምታደርገው ጥረት ሊደግፉ እንደሚገባ ያስረዳል።

ኢትዮጵያ በራሷ አቅም በምታመርታቸው የጦር መሳሪያ ምርቶች ደህንነቷን መጠበቅ መቻል አለባት የሚለው ወጣት ሳሙኤል፤ ይህ ካልሆነ በዙሪያዋ ብዙ ጠላቶች በመኖራቸው ከምንም ነገር በላይ ደግሞ የሀገር ሉዓላዊነት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ዘርፉ የሚመለከተው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለፈጠራ ሥራዎቹ ድጋፍ እንዲያደርግ ጠይቋል።

በኢትዮጵያ የተመረተ የሚል ምልክት ያለባቸው የወታደራዊ ምርቶች ለዓለም ገበያ የማቅረብ ራዕይ አለኝ የሚለው ወጣት ሳሙኤል፤ ከዚህ በተጨማሪ በኤሮስፔስ ዘርፉ ላይ የራሱን ድርሻ በመወጣት ለሀገሩ ሁልጊዜ የሚነገር ታሪክ ለማኖር ውጥን እንዳለው ይናገራል።

መንግሥት በየአካባቢው እንደ እርሱ ዓይነት የፈጠራ ዝንባሌ ያላቸው ወጣቶች ሥራቸውን ማጎልበትና ማሳደግ የሚችሉባቸውን የፈጠራና የቴክኖሎጂ ማዕከላት ቢፈጥሩ የተሻለ ሥራ መሥራት እንደሚቻል እና የቴክኖሎጂና የፈጠራ ሥራ በይበልጥ ድጋፍና ክትትል የሚያገኝበት መንገድ ቢኖር መልካም ነው ይላል።

የልጅነት ህልሙን ለመኖርና ሥራውን ለመሥራት ጥረት በሚያደርግበት ወቅት ከሚያጋጥሙት ተግዳሮቶች አንዱ ከአንዳንድ ግለሰቦች የሚሰጥ አሉታዊ አስተያየት ነው የሚለው ወጣት ሳሙኤል፤ በተለይም "ሚሳኤል እሠራለሁ ብለህ አትልፋ፤ የጦር መሳሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት የማይታሰብ ነው" የሚሉ ሰዎችን አስተያየት ለመስማት ጆሮ እንዳልሰጠ ይናገራል።

"ሁልጊዜ ችግሮች መልካም አጋጣሚ ይዘው ይመጣሉ ብዬ አምናለሁ" የሚለው ሳሙኤል፤ ሰው የራሱን አስተያየት ይሰጣል፤ መርጦ መውሰድ ደግሞ የግለሰቡ ኃላፊነት ነው። የትኛውም አሉታዊ የሰዎች ሃሳብ ደግሞ ትክክለኛ ግብ አስቀምጦ የተነሳን ዓላማ ያለው ሰው ከመንገድ ማስቀረት አይችልም ይላል።

በተደጋጋሚ "ለምን ደቦ የሚተኩስ ማሽን አትሰራም?" የሚል የሰዎች አስተያየት እንደሚደርሰው የሚናገረው ወጣት ሳሙኤል፤ እርሱ ግን "እኔ በሀገር ደህንነት ላይ የራሴን አስተዋጽኦ ለማበርከት ልሥራ ሌላው ደግሞ ደቦ የሚተኩስ ማሽን ይሰራ" የሚል ምላሽ በመስጠት ጉዞውን እንደቀጠለ ገልጾ፤ ሁሉም በተለያየ መልክ የራሱን ሚና መወጣት ከቻለ ሀገርን መለወጥ ከባድ እንዳልሆነ ይናገራል።

ወጣት ሳሙኤል እንደሚያስረዳው፤ የተለያዩ ሀገራት የሰው ሠራሽ አስተውሎትን በተመለከተ የተለያዩ ሥራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ። በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለመሳብ ጥረት እያደረጉ ነው። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ መንግሥት የነቃ ተሳትፎ በማድረግ አለበት። ምክንያቱም በሚመጣው ዘመን ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ለቴክኖሎጂ ሥራና ምርምር ትልቅ ትኩረት መስጠት የግድ ነው።

እንደ ቱርክ ባሉ ሀገራት ለወጣት የፈጠራ ባለሙያዎች የሚሰጠው ድጋፍ ጠንካራ እንደሆነና በዚህም የራሳቸውን የሰው ኃይል ተጠቅመው ውጤታማ እንደሆኑ የሚናገረው ሳሙኤል፤ ኢትዮጵያም ይህንን ልምድ በመውሰድ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶች ዘላቂነት ባለው መልኩ የምትደግፍበት አሠራር መዘርጋት እንደሚገባት ያስረዳል።

ኢትዮጵያ አቅም አላት። ብዙ መሥራት ትችላለች የሚለው ሳሙኤል፤ ነገር ግን የሚመለከታቸው አካላት በቴክኖሎጂ ዘርፍ በተገቢው መንቀሳቀስ ባለባቸው ልክ እየተንቀሳቀሱ አለመሆኑን ይናገራል። ይህ መቀረፍ አለበት፤ ምክንያቱም በዚህ ዘርፍ እየሠራ ያለው ወጣት የሚደግፈኝ አካል የለም ብሎ ሥራውን ተስፋ በመቁረጥ ማቆም የለበትም ይላል። በሌላ በኩል የሚደግፍ አካል ባይኖርም የራስን ጥረት ማድረግ እንደሚገባ ይገልፃል።

በመጨረሻም ወጣት ሳሙኤል ባስተላለፈው መልዕክት፤ ህልም ሁልጊዜ ዋጋ መክፈል ይኖረዋል፤ ፀንቶና ተግቶ በመሥራት የማይሳካ ነገር የለም ብሎ በማመኑ፤ ኢትዮጵያን በተለያየ ዘርፍ የማበልጸግ ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው ወጣቶች እንደመሆናቸው ለዓላማቸው መሳካት ባለመሰልቸት መትጋት አለባቸው ይላል።

# የምድር በረከት

# የማዕድን ሀብቶች ክምችት ልየታና ልማት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት የታደለች ታድላለች። የማዕድን ሀብቶቹም በሀገሪቷ በሁሉም አካባቢዎች የተለያዩ ማዕድናት በስፋት እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የወርቅ፣ የፖታሽ፣ የታንታለም፣ የሊትየም፣ የከበሩ ማዕድናት፣ የክሮማይት፣ የፎስፌት፣ የኒኬል፣ የጨው፣ የኢንዱስትሪ፣ የኮንስትራክሽን፣ የጂኦተርማል ኃይል፣ ለኢነርጂ ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት እና እጅግ አስፈላጊ የሚባሉ የማዕድን አይነቶች በሀገሪቱ እንደሚገኙ ከተለያዩ መረጃዎች መረዳት ይቻላል።

ሀገሪቱ እነዚህ ሁሉ የማዕድን ሀብት ይኑራት እንጂ ማዕድናቱን በጥናት በመለየትና በማልማት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ በኩል ብዙም አልሠራችበትም። የማዕድን ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፡ -እስካሁንም ሀገሪቱ ያላት የማዕድን ሀብት በዓይነትም ሆነ ክምችት መጠን በትክክል አይታወቅም፤ እነዚህ የማዕድን ሀብቶች ለማወቅ ጥናቶች በየጊዜው እየተካሄዱ ናቸው።

እስካሁን በተደረገው የአሰሳ ጥናት የአንዳንድ ማዕድናት የክምችት መጠን ተለይቶ ታውቋል። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ወርቅ ሲሆን፣ በቅርቡ የማዕድን ሚኒስቴር ይፋ ባደረገው መሠረት በሀገሪቱ ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። ከአንድ ቢሊዮን ቶን በላይ የሚገመት የብረትና ብረት ነክ የማዕድናት ክምችትም አላት። የድንጋይ ከሰልን ብንመለከትም ከግማሽ ቢሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ክምችት በሀገሪቱ ይገኛል።

ከዓለም ግዙፉ ያልለማ የፖታሽ ክምችት ካላቸው ሀገራት አንዷ መሆኗንም መረጃዎች ያመለክታሉ። በደናክል ተፋሰስ ውስጥ ከ26 ቢሊዮን ቶን በላይ የፖታሽ ሃብት ያላት ሲሆን፤ 540 ሚሊዮን ቶን የሚገመት የፖታሽ ክምችት አላት። የጂኦተርማል አቅሟም እስከ 10ሺ ሜጋ ዋት ይደርሳል ተብሎ ይገመታል።

በሀገሪቱ ይህን የመሰለ ከፍተኛ የማዕድን ክምችት እና የመልማት አቅም ያላት ቢሆንም፣ ለማዕድን ዘርፉ ትኩረት ሳይሰጥ በመቆየቱ ምክንያት ሀብቶቹን አልምቶ መጠቀም አልተቻለም። አሁን ላይ መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት ሀገሪቷ ያላትን የማዕድን ሀብት ክምችት አሰሳ በማድረግ የማዕድን ሀብቶቹ ለምተው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ ኢትዮጵያ የማዕድን ሀብቷን በማልማት የመጠቀም ሰፊ ዕድል እንዳላት ይገልጻሉ። ለእዚህ የመጀመሪያው ሥራ መሆን ያለበት የማዕድን ሀብትን ለይቶ ማወቅ መሆኑን ያመለክታሉ። የማዕድን ሀብቱ በየትኛው አካባቢ እንደሚገኝ፣ በምን ያህል መጠን ሊለማ እንደሚችል ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሠራበት ይገባል ሲሉ ተናግረው፣ በመቀጠልም የማዕድን ሀብቱ የሚለማበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ይህ ማድረግ ያስችል ዘንድ ባለፉት ዓመታት የማዕድን ዘርፍ የኢኮኖሚ ልማት ምሰሶዎች ተብለው ከተለዩ አምስት ዘርፎች አንዱ እንዲሆን ተደርጓል ሲሉም ጠቅሰው፣ ዘርፉ ለኢኮኖሚ ልማት አስተዋፅዖ የሚያበረክትና ለሀብት ፈጠራ ወሳኝ ተብሎ መለየቱንም አመልክተዋል።

የማዕድን ሀብቱ እንደ ሌሎች ዘርፎች እምቅ ሀብቶች ሀብት አመንጪ እንዲሆን በተለየ መልኩ የፖሊሲ ትኩረት ማግኘቱንም ሚኒስትር ዴኤታው ይገልጻሉ። ማዕድናት ከመድኃኒት ጀምሮ የተለያዩ ቁሳቁስ የሚመረትባቸው ግብዓቶች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በቂ ትኩረት ተሰጥቷቸው ቢሠራባቸው የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ከመሆን ባሻገር፣ ለግብርና፣ ለማኒፋክቸሪንግ እና ለሌሎች ዘርፎች ግብዓት በመሆን ለሀገሪቱ የምጣኔ ሀብት እድገት በብዙ መልኩ ሊጠቅሙ እንደሚችሉም አስታውቀዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት መነሻ በማድረግ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል። እስካሁን በማዕድን ዘርፉ ከተሠሩ ሥራዎች በሀገሪቱ ያሉ የማዕድናት መረጃዎች በማጥራት፣ በአነስተኛ፣ በመካከለኛ እና በከፍተኛ



የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ

ደረጃ ዘርፉን ለማልማት ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው። በአስር ዓመቱ እና በአምስት ዓመቱ የልማት እቅድ ላይ በተመለከተው መሠረት ዘርፉ ለአገር የሚያበረክተውን ሚና በሚለይ መልኩ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ ለኮንስትራክሽን ግብዓት የሚውሉ ማዕድናትን ድንጋይና አሸዋን ጨምሮ፣ ወርቅ፣ ኒኬል፣ ኮፐር፣ ማንጋኒዝ፣ ፖታሽ ፣የጌጣጌጥ ማዕድናት፣ ኢንዱስትሪ ማዕድናት፣ ታንታለም፣ ብረት እና ብረት ነክ ማዕድናት፣ በዘመኑ በጣም ተፈላጊ የሆኑ ማዕድናት እና የሌሎች ማዕድናት በተፈጥሮ ያላት ሀገር ናት። ለኃይል ማመንጨት በእጅጉ የሚፈለገው የድንጋይ ከሰል ክምችትም በስፋት ያላት ሲሆን፤ የድንጋይ ከሰሉን በማልማትም ለሲሚንቶ እና ለብረት ኢንዱስትሪዎች የኃይል ምንጭ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል።

በዓለም ላይ ሰፊ የጂኦተርማል ሀብት አላቸው ከሚባሉት ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ ተጠቃሽ መሆኗን አመልክተው፣ ኢትዮጵያን አቋርጦ የሚያልፈው ስምጥ ሸለቆ ያበረከተው አንድ አዲስ የተለየ ፀጋ የጂኦተርማል ኃይል ነው ሲሉ ይገልጻሉ።

በጂኦተርማል ኃይል ልማት 11 የሚጠጉ ኩባንያዎች ገብተው እየሠሩ ይገኛሉ ሲሉም ጠቅሰው፣ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ ሦስት የሚሆኑት ኩባንያዎች ወደ ልማት ተሸጋግረው የኃይል አቅርቦቱን ለማከናወን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ጋር በመነጋገር ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

ከእነዚህ በተጨማሪም በሀገሪቱ የኢነርጂ ማዕድን የሚባሉት የተፈጥሮ ጋዝ እና ነዳጅ ሀብቶች እንዳሉም ይገልጻሉ። እነዚህን ሀብቶች በማልማት ረገድም በፍለጋ ሥራ ላይ የተሠማሩ እና ፍለጋቸውን እያጠናቀቁ ያሉ ኩባንያዎችም መኖራቸውን አስታውቀዋል፤ በወርቅ ማዕድን ልማትም የተሠማሩ በርካታ ባሕላዊና ከፍተኛ የወርቅ አምራች ኩባንያዎች እንዳሉ አመላክተዋል ።

‹‹የማዕድን ፍለጋ ሥራ ረጅም ዓመታት ይወስዳል›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ባለፉት 15 ዓመታት በተደረጉት የአሰሳና የፍለጋ ሥራዎች ከ517 ቶን በላይ የወርቅ ሀብት ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል ብለዋል። የወርቅ ሃብቶቹም በሚቀጥሉት 20 እና 25 ዓመታት እንደሚለሙ ጠቅሰው፤ ሀብቶቹ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ ኦሮሚያና ትግራይ ክልሎች እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

የወርቅ ማዕድን ልማት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ልማት አዲስ ዕድል ይዞ የሚመጣ ነው ሲሉ የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በባሕላዊ መንገድ ሲመረት የኖረው የወርቅ ምርት አሁን በተለያዩ ማሽኖች እገዛ ወደ ማምረት እየተገባ መሆኑን አስታውቀዋል፤ ይህን ተከትሎም ምርቱን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ መቻሉንም ይገልጻሉ።

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የወርቅ ልማቱን በኩባንያ ደረጃ ለማካሄድ አንድ ኩባንያ በግንባታ ሂደት ላይ መሆኑ ይታወቃል። በክልሉ ኩርሙክ አካባቢ እየተገነባ ከሚገኘው ከዚህ የወርቅ ማውጫ ፋብሪካ በተጨማሪ፣ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት አራት የወርቅ ማውጫ ፋብሪካዎች እንደሚገነቡም ይጠቅሳሉ። እነዚህ ፋብሪካዎችም በወለጋ፣ በቤንሻንጉል፣ በጋምቤላ እና ትግራይ ክልሎች ይገነባሉ ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ የማዕድን ሀብት የመጀመሪያ ሥራ የሚባለው የማዕድን ፍለጋ ነው። የማዕድን ፍለጋ ሥራው ከሦስት ዓመት እስከ አስራ አምስት ዓመት ሊቆይ ይቻላል። ይህም ከማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት አንጻር የሚታይ ዓለም አቀፍ አሠራርን የተከተለ ነው።

በሀገሪቱ የማዕድን ልማት ሥራው እስካሁን በተበጣጠሰ መልኩም እየተሠራ ቆይቷል። ከለውጡ በፊት የማዕድን ሀብቶችን የመለየት ሥራ በተለያዩ ኩባንያዎች ሲሠራ ነበር። አሁን ላይ ኩባንያዎቹ የፍለጋ ሥራቸውን ጨርሰው ወደ ልማት እየተሸጋገሩ ይገኛሉ።

በአሁኑ ወቅትም በፌዴራልና በክልል መንግሥት ቅንጅት የፍለጋ ጊዜያቸውን ጨርሰው ወደ ልማት ምዕራፍ የተሸጋገሩ የወርቅ ኩባንያዎችን ወደ ልማት ለማስገባት ርብርብ እየተደረገ መሆኑን ሚኒስትር ዴኤታው ጠቁመዋል።

አቶ ሚሊዮን እንዳብራሩት፤ በማዕድን ዘርፉ በ2016 በጀት ዓመት ባለፉት ስምንት ወራት የተለያዩ ማዕድናት ለውጭ ገበያ ተልከዋል፤ ወርቅ ከሁለት ሺህ 673 ኪሎ ግራም በላይ፣ ታንታለም ከ66 ቶን በላይ፣ ሊቲየም ኦር ከ11 ሺህ 176 ቶን በላይ ለውጭ ገበያ ቀርበዋል። በተጨማሪም ከ99 ሺህ 021 በላይ ቶን የጌጣጌጥ እንዲሁም 29 ሺህ 281 ቶን በላይ የኢንዱስትሪ ማዕድናት ለውጭ ገበያ ማቅረብ ተችሏል።

በበጀት ዓመቱ ባለፉት ስምንት ወራት ከማዕድን ዘርፍ 252 ነጥብ 15 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉንም ጠቅሰው፤ ገቢው ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ጭማሪ ያሳየ መሆኑንም ጠቁመዋል።

‹‹አሁን ላይ በማዕድናት ፍለጋ ሥራ ላይ በስፋት እየተሠራ ነው›› መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል፤ ዘርፉ በጥንቃቄ መመራት እንዳለበት ተናግረው፣ ኩባንያዎችም ሆኑ ኢንቨስትመንቱ ላይ መሳተፍ የሚፈልጉ አካላት ሲመለመሉ በዘርፉ ላይ ያላቸውን ልምድ እንዲታይ እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

‹‹ይህ እንዲሆን ያስፈለገበት ምክንያት የማዕድኑ ዘርፍ እንደ ሌላው ዘርፍ የተወሰነ ሥራ ብቻ ተሠርቶበት ወደ ልማት የሚገባበት ዘርፍ ስላልሆነ የፍለጋ ሥራው ከሦስት ዓመት እስከ አስር ዓመት ከፍ ሲልም እስከ 15 ዓመት ከፍተኛ ፋይናንስ መደቦ መሥራትን የሚጠይቅ ስለሆነ ነው›› ሲሉ አብራርተዋል። ‹‹ይሄ ደግሞ በአጭር ጊዜ ፈጥኖ ሊደርስበት የማይችልበት ሁኔታ ስለሚኖር ኢንቨስትመንቱ ላይ መሠማራት የሚፈልጉት ባለሀብቶች ያላቸው የመነሻ ፋይናንስ፣ ቴክኒካል እና የሰው ኃይል አቅም ጭምር የመለየትና ሥራ ይሠራል›› ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳብራሩት፤ በሀገሪቱ እስካሁን ድረስ በዓለም ላይ ቁጥር አንድ ከሚባሉት መካከል አንዱ የሆነ ኩባንያ ጀምሮ ትላልቅ ኩባንያዎች በማዕድን በፍለጋ ላይ ተሠማርተው ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል አንዳንዶቹ የፍለጋ ሥራቸውን አጠናቅቀው ወደ ምርት ተሸጋግረዋል። እስካሁን የተሠራው ሥራ በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ እነዚህ ኩባንያዎች ወደ ውጤታማነት ማሸጋገር ይገባል።

ሀገሪቷ ከማዕድን ዘርፍ ባላት አቅም ልክ ተጠቃሚ እንድትሆን ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ የማዕድን ዘርፍ ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር እንደሚያስችልም ያመላክታሉ። በማዕድን ዘርፍ እስከ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዜጎች በቀጥታ በዘርፉ ላይ ተሠማርተው እንደሚገኙ አስታውቀዋል። በተዘዋዋሪ ደግሞ ከ7 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ዜጎች ከዘርፉ ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኙ አመላክተዋል።

እንደ አቶ ሚሊዮን ማብራሪያ፤ የዘርፉ ተግዳሮት የሆነውን ሕገወጥነት ለመከላከል ከፌዴራል እስከ ክልል ያለው ተቋማት ተቀናጅቶ እንዲሠሩ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የሚመራ ሀገራዊ የማዕድን ካውንስል ተቋቁሞ ወደ ተግባር ገብቶ እየሠራ ይገኛል። ካውንስሉ የክልል ምክትል ፕሬዚዳንቶች፣ ሚኒስትሮችም የተካተቱበት ስለሆነ ከክልልና ከፌዴራል ያሉ አካላት በቅንጅት ሥራዎችን የሚሠሩበት ነው።

የማዕድን ካውንስሉ ቅንጅታዊ አሠራሮችን መከተል በማዕድን ዘርፍ ውጤት ያመጣል ተብሎ ይታሰባል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በዘርፉ ተንሰራፍቶ ያለውን የኮንትሮባንድ ንግድና ሕገወጥነት ለመከላከልም የክልልና የፌዴራል የፀጥታ መዋቅሩ ከፖለቲካ አመራሩ ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራበትን ዕድል ይፈጥራል ሲሉ አብራርተዋል።

ዘርፉን ለመምራት እንዲቻል የተለያዩ ሥራዎች በቅንጅት መሠራት እንዳለባቸው ጠቅሰው፣ በዚህ ረገድ የሚሠሩ ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ መንግሥት ተገቢውን እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ጠቁመዋል። እነዚህ ተጠናክረው ወደ ውጤት እየተቀየሩ ሲመጡ ለዘርፉ ምቹ ሁኔታ እየተፈጠረ ይሄዳል ተብሎ ይታሰባል ሲሉ ያስረዳሉ።

‹‹ሕገወጥ እና የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ የሀገርን ጥቅም ብቻ አይደለም የሚያሳጡት፤ ለሀገራዊ ሠላምና መረጋጋት ጭምር ከፍተኛ ጠንቅ ናቸው›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የማዕድን ካውንስሉ መቋቋም ሀብት እንዳይመዘበር፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር እንዳይካሄድ እና ሠላምና ደኅንነት እንዲኖር ያደርጋል ይላሉ።

ከዚህ በተጨማሪም በሚቀጥሉት ዓመታት ወርቅ ለማውጣት ለሚገነቡት ፋብሪካዎች የሚፈልጉት መሠረተ ልማት እና ከውጭ የሚገቡ ትላልቅ ማሽኖች ለማስመጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም አስታውቀዋል። ይህም በተለያዩ ተቋማት ላይ ሲያጋጥሙ የቆዩ ውጣ ውረዶችን በማስቀረት ሥራዎች በተቀናጀ መልኩ እንዲፈጸሙ ያስችላል ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው ለዚህም ለሚ ሲሚንቶ ፋብሪካ በአብነት ይጠቅሳሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ ለሚ ሲሚንቶ ፋብሪካ የሀገሪቱ ግዙፍ ፋብሪካ ነው። ይህ ፋብሪካ እውን እንዲሆን ፋብሪካው ሲገነባ ጀምሮ ተቀናጅቶ ለመሥራት ጥረት ተደርጓል። አሁን ፋብሪካው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሥራ ዕድልና አጠቃላይ ኢኮኖሚ ሊያንቀሳቅስ የሚችል አንድ ትልቅ አቅም ፈጥሯል። በቀጣይ በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገነቡ ፋብሪካዎችን የመሠረተ ልማት ችግር እንዳያጋጥም ቅንጅታዊ አሠራር በመዘርጋት ከወዲሁ ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ መሆኑን አስገንዝበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ወዲያ ወዲህ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጽ)**

በህይወቴ የምቆጭባቸው ሁለት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው በነሶቅራጠስ ዘመን አለመወለዴ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በእኔ ዘመን ሶቅራጠስን መሳይ ሰው አለመፈጠሩ ነው። የኦሾና የሶቅራጠስ ስለህይወት ያላቸው እይታ ይማርከኛል። ከእየሱስ ጋር አብረው ህይወትን የፈጠሩ ይመስል ህይወት ማለት እንዲህ ናት፣ መኖር ማለት ይሄ ነው ሲሉ በሰሚ ልቦና ውስጥ ጉጉት ይፈጥራሉ። ግን እንዴት ህይወት ገብቶኝ ሱሰኛ ሆንኩ? ግን እንዴት ራሴን ማፍቀር አቃተኝ? ያልመለስኩት ጥያቄዬ ነው።

አሁን አሁን ቁጭቴ ወደሶስት ከፍ እያለ መጥቷል። እየሱስ ምድር ላይ ሳለ ብኖር እላለው። በከብቶች በረት ሲወለድ፣ ውሀ ቀድቶና እንጨት ለቅሞ እናቱ ማርያምን ሲያገለግል፣ በጭቃ ህያው ወፍ ሲሰራ ባየሁት እላለው። ወደ ገሊላ ሲያቀና፣ በዶኪማስ ቤት ውሀውን ወደ ወይን ሲቀይር ብታደም እላለው። የቢታኒያ ድንጋዮች ሲያመሰግኑት፣ በበርሀ ውሀ ሲያፈልቅ፣ በደብረታቦር በብርሀን ባየው እመኛለው። መካናን ሳራን ሲያስቅ፣ ፈርኦንን ሲቀጣ፣ ለአብረሀም ቃል ሲገባ፣ ኖህን ከጥፋት ውሀ ሲያድን ጎኑ ብሆን እላለው። በጌቴሴማንያ በአትክልቱ ስፍራ፣ በጥብሪያዶስ በባህሩ ዳር፣ በዳናው ጥላ በጌርጌሴኖን አብሬው ቆሜ ቢሆን፣ ጣሊታን ከሞት ሲያስነሳ፣ መቅደላዊት በእንባዋ እግሩን ስታጥብ፣ የሳምራዊቷ ሴት ሲያነጋግር ሰምቼ ቢሆን። በአህያ ውርንጭላ ሲጓዝ፣ የማርያም እህት ማርታ መልካም እድልን መርጣ እግሩ ስር ስታርፍ፣ ዘኪዮስ ሊያየው ዛፍ ላይ ሲወጣ፣ ከተከተሉት ከአምስት የገበያ ህዝብ አንዱን ብሆን። በእለተ አርብ አሳ ካበላቸው አምስት ሺ እንግዶች አንዱን ሆኘ ብሆን ያምረኛል። እንደዛች ለአስራ ሁለት አመት ደም እንደሚፈሳት ሴት ቀሚሱን ዳስሼው ቢሆን፣ እንደጰርጠሚዮስ የናዝሬቱ እየሱስ ሆይ ብለው፣ እንደ ሀር ሻጪዋ ሊዲያ በድምጹ ልቦናዬ ቢከፈት አስባለው።

እያሱ ጸሀይን ሲያቆም፣ ኤሊያስ ዝናብን ሲገስጽ፣ ሙሴ ባህር ሲከፍል፣ ዳዊት ጎልያድን ሲጥል፣ ደሊላ ሳምሶምን ስትረታ፣ ቤርሳቤህ ከኦርዮን ስትሸሽ፣ ሄሮዲያዳ አንገት ስታስቆርጥ፣ አስቴር ሀማስን ስትሰቅል፣ ሜልኮል ስትዘባበት፣ አዚያ ሲቀሰፍ፣ ሩት ስትቃርም፣ ሶስና ከእደረበና ስትድን፣ አፎሚያ ሲከብር፣ እስቂያስ ሲያነባ፣ አጋር ስትሰደድ፣ አናኒያና ሰጲራ ሲዋሹ፣ አክአብ ሲዝት፣ ኤልዛቤል ሲያቅራራ፣ ዮሴፍ ሲሸጥ፣ አዳም ሲያንቀላፋ ሰው ሆኘ ኖሮ ስል እመኛለው። ቃየል በወንድሙ ላይ ሲነሳ፣ ሄዋን ሉድ እና ቅሌማን ስትወልድ፣ ታራ ጣኦት ሲያመልክ፣ ስምኦን አይኑን በወስፌ ሲያፈስ፣ ፌቨን ወደቆረንቶስ ስትላክ፣ ሀናና ፍናና ሲነቋቆሩ ባይና ብሰማ። ጴጥሮስ ሲክድ፣ ይሁዳ ሲያስመስል፣ በርባን ሲፈታ፣ ቬሮኒካ የጌታን ደም ስትጠርግ ህይወት ኖሮኝ ቢሆን እላለው።

ጴጥሮስን ከቀራጭነት፣ ስሞንን ከአሳ አጥማጅነት፣ ማቲያስን ከውንብድና ወዳጁ እንዳደረገ እኔንም ከሱሰኝነ አውጥቶ ደቀመዛሙሩ ቢያደርገኝ ስል ይሆኑ እመኛለው። በዚህ አለም ላይ እየሱስን እንደመከተል ምን ጥበብ አለ? ግን እኮ በራሴ ዘመን ላይም እየሱስን መፍጠር እችላለው። ያን ማድረግ ለምን አቃተኝ? ያኔ ብቻ አይደለም እየሱስ ዛሬም ጌታ ነው። ለምን በራሴ ውስጥ እሱን መፍጠር ተሳነኝ? ሰው ከምኞት ወጥቶ ላመል ፈቀቅ እስካላለ ድረስ የትናንት ምርኮኛ ነው። ቅርቡ እየሱስ ርቆኝ በማይሞትበት አለም ላይ እየኖርኩ የተወለደበትን ዘመን እናፍቃለው። እሱ እኮ ዛሬም አዲስ ..ዛሬም ስለእኛ ጎለጎታ ነው ብሎ የሚነግረኝ አማኝ አጣሁ። ለነገሩ ቢነግሩኝስ መች ሰምቼ። ክርስትና የተነሳሁበት የአርባ ቀን አጥቢያዬ አጠገቤ አይደል። ቄሱን ሳልሰማቸው መቼ ቀርቼ አውቅና። ያን በስብከቱ ጉድ የተባለለት ሰው ጆሮ ግንዴ ላይ አይደል? መች ከእውነቴ አራቁኝ። መች ከምኞቴ አሸሹኝ። መች ወደእየሱስ አደረሱኝ። አውቆ የተኛን አሉ..

መርፌ ሲለግም መች ቅቤ ይወጋና?

እንደልማዴ የማጨሰውን ሲጋራ በመሀል ጣቴ ሰክቼ፣ እንደእኔ ግራ የገባት የምትመስለውን የከሰዓት ጀምበር ተከትዬ እግሬ ወደወሰደኝ ወደሆነ ቦታ ተራመድኩ። ሰው ግን ሀሳብ ይጠፋዋል? ድንገት መጥቶ ሀሳብ ይጠፋኛል። ሃሳብ ቢኖረኝ ኖሮ እግሬ እንደመራኝ አልሄድም ነበር። እየሱስን ያልደረስኩበት ያለሀሳብ እግሬ እንደመራኝ እየተጓዝኩ ይሆን? አዎ እንደዛ ቢሆን ነው። እንደዚ ካልሆነ ሌላ ምንም አይሆንም። አንዳንድ ልማዶች የአለመርባት አዲስ ዓመቶች ናቸው። ሰው በሀሳብ እግሮቹን ካልመተረ መድረሻው የለውም አልኩ።

ብቻ እግሬን ተከትዬ ራቅ ብዬ ሄድኩ። የሲጋራዬ እድሜ አልቆ የመጨረሻ ጭሴን ወደሆዴ ስቤ ሌላ አቀጣጠልኩ። እየሱስን በእንደእኔ አይነቱ ወንበዴ ውስጥ ፈልጎ ማግኘት ፓስፊክ ውቅያኖስን በማንኪያ ጨልፎ ማጉደል መስሎ ታየኝ። ማን ነበር ያ በትንሽ ጽድቅ ከማንም ቀድሞ ገነት የገባው? ማን ነበረች ያቺ ስትዘሙት ኖራ በእግዜር ጻድቅ አይኖች የታየችው? ገድለ አሪት..ገድለ ሀዲሴን እንዳላበላሸ በሀሳቤ መሀል እየተሰነቀረ..አንተ እኮ ማለት እያለ ያመጻድቀኝ ጀመር።

ያለሀሳብ መጓዝ በመኖር ውስጥ ያለ የሰው ልጅ ያልደረሰበት ምቹ የነጻነት ስፍራ መስሎ ታየኝ። ግን አይደለም እንደማሰብ ጉልበታምና ሞገሳም ነጻ አለም አላየሁም። ገብቶኝ እንኳን ልወዳጀው አቅም አጣሁ። አለማሰብ አለማወቅ ነው። ዝም ብሎ መኖር..ዝም ብሎ መሞት። ህይወትን የምናምርባት በማሰብ ውስጥ ነው። ሞትን የምንንቀው በስልሳሌ ውስጥ ነው።

ባለማሰብ ብዙ ተጉዤ መድረሻዬን አንድ ስፍራ አደረኩ። ሰፊ ግቢ ውስጥ በቅለው የግቢውን ውጪ አውራ ጎዳናውን ባጠሉ ዛፎች ስር። ጥላው ያምራል..በተደራረቡና በተቃቀፉ ረጃጅም ዛፎች የተሰራ ጥላ ነው። የአስፓልቱ ግማሽ ድረስ ተወርውረው ጥላማ አድርገውታል። የግንቡን አጥር ተደግፋ አንዲት ሴት ቆማለች። አለማሰቤ ሀሳብ ጀመረ። ምንም እንኳን ተጉዤ ባልደርስበትም ከክርስቶስ ምክረ ሀሳብ ማፈንገጥ አልወድም። እንዲህ ስል ጻድቅ ነኝ እያልኩ ሳይሆን ቢሆንለት ለእውነት ቅድሚያ የሚሰጥ ሰው ነበርኩ እያልኩ ነው። ከጎለጎታ በፊትም ሆነ በኋላ የእየሱስ ህገ ሥርዓት መነሻ ያደረገው ፍቅርን ነው። አቅም ኖሮኝ ብችል እንደእየሱስ ጠላቶቼን ሁሉ በፍቅር የረታ መሆን እፈልግ ነበር። ግን አልቻልኩም..የምችለው አንድ ነገር ነው አቅም አጥቼ እንዳልጠላ መሆን።

ፊት ለፊቴ አንዲት ጉብል የቆመችበት ጥላ..ጥላው አማረኝ። ከጸሀይ ወደጥላ ልብ ላይ የሚያርፍ የሆነ መንፈስ አለው..። ያ መንፈስ አረፈብኝ። ሲጋራዬን እያቦነንኩ ከወጣቷ አጠገብ ሄጄ ቆምኩ። ለትዝብት በሰሉ አይኖች ፊትለፊት ጎዳናውን ትቃኛለች። ሀሳብ ብትዘራብኝ ስል ተደናብሬ ሄጄ ከሀሳቧ ላደናቅፋት ፈለኩ።

ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም ስል ከሲጋራዬ አንድ ጊዜ ስቤ ‹እንኪ! ስል ዘረጋሁላት።

እንደዛ ቀን አልተገላመጥኩም። ለምላሹ ብዙ መልካም ነገሮች ነበሯት። እሷ ግን ግልምጫን አስቀድማ እንዳልነበረ አደረገችኝ።

አልተከፋሁም። ‹ከሌሎች ጋር ለመኖር ብዙ አማማራጮች አሉን። እንደመልካም አንደበት ግን ጥሩ አማራጭ የለንም› ስል ምንም እንዳልመሰለኝ እንድታውቅ በዛውም እንድትማር ቃል ወረርኩላት።

**‹የሰጠኸው እንደሚሰጥህ አታውቅም?**

**‹የሰጠውሽ መጥፎ መሆኑን በምን አወቅሽ?**

‹የሚረቡ ወንዶች ጣታቸው መሀል እስክሪፕቶ እንጂ ሲጋራ አይዙም› ብላ ወደትዝብቷ ተመለሰች።

ኩምሽሽ አልኩ። ‹እኔ ያለኝን ነው የሰጠሁሽ› ስል ድንጋጤዬን ለመደበቅ ሞከርኩ።

‹ያሉን ነገሮች ሁሉ የማይጠቅሙን እንደሆኑ አታውቅም?

‹አልስማማም። ካጣናቸው እና ከሌሉን ነገሮች እንደሚበልጡ ነው የማውቀው።

‹እንደዛም ማሰብ ትችላለህ። ከሁሉም የሚበልጠው መልካም አንደበት ነው ስትል የሰማሁ መሰለኝ..?

‹አዎ ሰምተሻል..!

‹እንግዲያውስ ከሁሉም የሚበልጥ ሌላ ነጻ አውጪ እውቀት እንዳለም ጨምርበት› ብላኝ ትታኝ ሄደች። ከጥላው ወጥታ ጸሀዩዋ ላይ ስትማገድ የሆነ ነገር ቅር ቅር አለኝ። በወጣችበት ቅጽበት ተሲያቷን ትታ ጀምበር እንደጌታ የስቅለት ቀን ጨላለመች።

ወደእየሱስ ታደርሰኝ እንደሁ ስል ተከተልኳት። አስወጣችን እንጂ ከመች ጀምሮ ነው ሴት ወደገነት የምታስገባው? አንዱ ልቤ እንዲህ ይለኛል። ቢሆንም መራመዴን አላቆምኩም።

# ዓለም አቀፍ

## ዩክሬን ሩሲያ ላይ ያነጣጠሩ መረጃ መንታፊዎችን ሸለመች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ ላይ የሳይበር ጥቃት ያደረሰ የመረጃ መንታፊዎች ቡድን ከዩክሬን ጦር የዕውቅና ሽልማት ተበረከተለት። ‘ዋን ፊስት’ የሚባለው ቡድን የሩሲያ የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎችን እና ካሜራዎችን በመጥለፍ መረጃዎችን ሰርቋል።

ዕውቅናው አወዛጋቢ እና ዘመናዊውን የጦርነት አካሄድ ያሳያል ተብሏል። መንግሥታት ሲቪል መረጃ መንታፊዎችን የሚያበረታቱበት አካሄድም ስጋት የጫረባቸው በርካቶች ናቸው።

ከመረጃ መንታፊዎቹ አንዱ የሆነው “ቮልቴጅ” ሥራውን የሚያጧጡፈው አሜሪካ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ነው።

በትክክለኛ መጠሪያ ስሙ ክሪስቶፈር ኮርትራይት የሚባለው መረጃ መንታፊ የአይቲ ባለሙያ ሲሆን መቀመጫውን ሚቺጋን አድርጓል።

የ53 ዓመቱ መረጃ መንታፊ ለዩክሬን ያደረገው ጥረት ዕውቅና በማግኘቱ መደሰቱን ገልጿል።

‘ዋን ፊስት’ ዩናይትድ ኪንግደም፣ አሜሪካ እና ፖላንድን ጨምሮ ከስምንት ሀገራት የተወጣጡ የመረጃ መንታፊዎች ያቋቋሙት ነው። በደርዘን የሚቆጠር የሳይበር ጥቃት ያደረሱ ሲሆን ደስታቸውንም በማህበራዊ ሚዲያ ይገልጻሉ።

"ለሠራዊቱ ዕድገት እና ወሳኝ እንቅስቃሴ ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ" የሚሉት የምስክር ወረቀቶቹ ለሁሉም አባላት ተልከዋል። የዩክሬን የአየር ኃይል አዛዥም ፊርማቸውን አኑረውበታል። የዩክሬን መከላከያ ሚኒስቴር ከቢቢሲ ለቀረበለት ጥያቄ ምላሽ አልሰጠም።

ዩክሬን ወደ ጦርነት ከገባች ጀምሮ በአወዛጋቢ ሁኔታ በጎ ፈቃደኛ መረጃ መንታፊዎች ሩሲያን እንዲያጠቁ እያበረታታች ትገኛለች። ኦፊሴላዊ ሽልማቶችን ለሌላ ሀገር ዜጎች መላኳ አወዛጋቢ ከመሆኑም በላይ የዘመኑ ማሳያ ተደርጎም እየታየ ነው።

ዩናይትድ ኪንግደም እና አሜሪካን ጨምሮ በርካታ ሀገራት ለመልካም ነገር መረጃ ለሚመነትፉ ኦፊሴላዊ ሽልማት ቢኖራቸውም ለጥፋት እና ምናልባትም ለወንጀል የሚደረግን የመረጃ ምንተፋ ዕውቅና በመስጠት ዩክሬን የመጀመሪያው እንደሆነች ይታሰባል።

በዩክሬን እና በጋዛ ግጭት ውስጥ የተስፋፋውን የምንተፋ ተግባር ተከትሎ ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ኮሚቴ (አይሲአርሲ) የሲቪል መንታፊዎችን በመጠቀም እና ማበረታታት ዙሪያ ባለፈው ጥቅምት ማስጠንቀቂያ አውጥቷል። የጄኔቫ ስምምነቶች ላይ የተቀመጡትን የጦርነት ሕጎች እንዲተገበሩ በማለትም አትሟቸዋል።

ዩክሬን ለውጭ መረጃ መንታፊዎች የሰጠችው ሽልማት ችግር ሊፈጥር ይችላል ሲሉ የሳይበር ደህንነት ፍልስፍና ደራሲ የሆኑት ዶክተር ሉካስ ኦሌይኒክ ተናግረዋል።

“ሽልማቶችን መስጠት በወታደሮች እና በሲቪሎች መካከል ያለውን ልዩነት የበለጠ ሊያደበዝዝ ይችላል። ዓለም አቀፉ ቀይ መስቀል በጦርነት ውስጥ የሲቪሎችን ተሳትፎ ለመገደብ እና ለማቆም ያቀረበውን ጥሪ ሊያኮስምነው ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ መሸርሸር በረጅም ጊዜ አደገኛ ውጤት ይኖረዋል” ብለዋል።

ዶ/ር ኦሌይኒክ አክለውም ሳይበር ጥቃት እንደ ጦርነት መቆጠሩ እና ማንም ሰው በበይነ መረብ ትግሉን መቀላቀል የሚችልበት ዕድል መኖሩ “የዘመናችን ማሳያ” ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሩሲያን ዩክሬንን በወረረችበት ወቅት መረጃ መመንተፍ የጀመረው ክሪስቶፈር፤ ለዓላማው ማደሩን እና ብዙ መስዋዕትነት መክፈሉን ይገልጻል።

“ለዚህ ብዬ ሥራዬን አጥቻለሁ። ዩክሬን እንድታሸንፍ ህይወቴን በሙሉ የቆጠብኩትን ገንዘብ አጥፍቻለሁ።



ሽልማት እውነተኛ የሞራል ማበረታቻ ነው" ሲል ከመኖሪያ ቤቱ ቢሮ ሆኖ ገልጿል።

ሽልማቶቹ የትኞቹ የሳይበር ጥቃቶች በጣም ጠቃሚ እንደሆኑ አይገልጽም። ቮልቴጅ ግን እጩዎች እንደሆኑ የሚያስባቸው ሦስቱን ነው።

በሩሲያና ዩክሬን መካከል ጦርነቱ እንደተጀመረ ዋን ፊስት በዩክሬን የሚገኙ በመቶዎች የሚቆጠሩ የደህንነት ካሜራዎችን አካላዊ እና የሳይበር ደህንነት ሲለይ ለወራት አሳልፏል።

በኋላም ካሜራዎቹን ተጠቅመው የሩሲያ ኃይሎች የዩክሬን ወታደሮችን ለመከታተል እየተጠቀሙባቸው እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። በዚህም ቡድኑ ካሜራዎቹን ከሥራ ውጪ እንዲሆኑ እገዛ አድርጓል።

በሩሲያ ቁጥጥር ስር በምትገኘው ክሪሚያ የሚገኙ ካሜራዎችን ሰርጎ በመግባት የሩስያ ታንኮችን እና መሣሪያዎች ድልድይ ላይ ሲንቀሳቀሱ ያሳየውም ዋን ፊስት ነው።

የኦክስፎርድ ኢንፎርሜሽን ላብስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና የቻተም ሃውስ ሳይበር ፖሊሲ ጆርናል አዘጋጅ የሆነችው ኤምሊ ቴይለር የምንተፋ ሽልማቶች የበጎ ፍቃደኞች የሳይበር ጥቃት በግጭቶች ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ የነበረውን እሳቤ የሚቀይር እንደሆነ ይስማማሉ።

## ነፃ ሃሳብ

# በስመ አራዳ ለዘመናት ድህነት ተጭኗቸው የቆዩ ሰፈሮች

**አሲሴሮ**

ከተመሠረተች ከ135 ዓመት በላይ የሆናት አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች መናኸሪያ፤ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የአፍሪካ መዲና እና የተለያዩ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ተቋማት መገኛ ነች። ከ90 በላይ ኤምባሲዎችን በማቀፍም በዓለም ላይ ካሉት ጥቂት የዲፕሎማቲክ ማዕከል ከሆኑ ከተሞች ውስጥ ግንባር ቀደሟ ነች።

ይህም ሆኖ ግን በመሀል ከተማዋ ከተሠሩ ዘመናትን የተሻገሩት ቤቶች /መንደሮች/ የሚያድሳቸው ጠፍቶ በእርጅና ምክንያት ጎብጠው፤ ግድግዳዎቻቸው ፈራርሶ፤ ጣራዎቻቸው ወይቦ የከተማዋን ውበት ሆነ የነዋሪዎቹን ሕይወት አስቸጋሪ አድርገውታል።

በእነዚህ ቤቶች ውስጥ በበጋም ሆነ በክረምት መኖር ስቃይ ነው። ቤቶች ከተማዋ ስትቆረቆር ጀምሮ የነበሩ በመሆናቸው የሚያፈርሳቸው አካል ባይኖር በራሳቸው እየፈረሱ ስለመሆናቸው የሚኖሩባት የሚመሰክሩት የአደባባይ እውነት ነው።

አብዛኞቹ ቤቶች ባለአንድ ክፍል በመሆናቸው ለነዋሪዎቹ መኝታም ምግብ ማብሰያም ናቸው። እናትና አባትን ጨምሮ ልጆችም ይህችኑ አንድ ክፍል ይጋራሉ፤ ይህም በራሱ በልጆች አስተዳደግ ላይ የሚኖረው አሉታዊ የሥነልቦና ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በእነዚህ ቤቶች ገበና መደበቅ የሚባል ነገር የለም። ሰዎች የግሌ የሚሉት ነገር የለም። ምግቡም መኝታውም ሌላም ሌላም ነገሩ በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ስለሚከወን ሁሉም ነገር የአደባባይ ሚስጢር ነው። ባልና ሚስት እንኳን የግል ነጻነት የላቸውም።

ሰፈሮቹ ችምችም ብለው በተሠሩ ቤቶች የታጨቀ፤ ከዘመኑ ጋር ያልዘመኑ፤ ከ135 ዓመታት በፊት ከነበሩበት በከፋ ሁንታ ያሉ እና በአሁኑ ወቅት ያለውን የአኗኗር ሁኔታ የማይመጥኑ ናቸው። አብዛኞቹ ቤቶች አንድ መጸዳጃ ቤትን ለሰላሳ፤ ለአርባ የሚጠቀሙ ብዙዎችም መጸዳጃ ቤት የሌላቸውና በየጥጋጥጉ ለመጠቀም የተገደዱ ዜጎች የሚኖሩባቸው ናቸው።

እነዚህ አካባቢዎች የአዲስ አበባን የኋሊት ጉዞ የሚያሳዩ፤ ከተማዋ ተመልካች የሌላት ስለመሆኑ ተጨባጭ መገለጫዎችም ናቸው። ጎዳና ተዳዳሪነት፤ ሴተኛ አዳሪነት፤ ማጅራት መቺነትና የመሳሰሉት ኢ ሞራላዊ እና ወንጀል ነክ ድርጊቶች የሚፈጸምባቸው፤ የቁማር፤ የጫት፤ የሺሻ እና የአረቄ ቤቶች መገኛም ናቸው።

በእነዚህ አካባቢዎች መሸት ሲል በቀላሉ ወጥቶ መግባት አይታሰብም። እነ ዶሮ ማነቂያ፤ እሪ በከንቱና ውቤ በረሃ የመሳሰሉ ሰፈሮች መጠሪያቸው የሚናገረውም ይህንኑ ነው። ፒያሳም ቢሆን ስሙ የደመቀ ቢሆንም በገቢር ያለው እውነታ ግን ስሙን የሚመጥን ገጽታ የተላበሰ አይደለም። አካባቢዎቹ ምንም ዓይነት ዘመናዊነት የማይታይባቸው ኋላቀር አካባቢዎች ከመሆናቸውም በላይ በስመ አራዳ ለዘመናት ድህነት ተጭኗቸው የቆዩ ናቸው።

ስምና ግብር በተራራቀበት በእነዚህ አካባቢዎች ሰዎች በአንዲት ክፍል ውስጥ ቆጥና ምድር ሰርተው፤ መጸዳጃ ቤት ተጋርተው፤ በአንዲት ክፍል አስር፤ አስራ አምስት ሆነው ተደራርበውና ተነባብረው የሚኖሩባቸው የድህነት ጥግ የሚታይባቸው የከተማችን አካል ናቸው።

ይህ አልበቃ ብሎ አካባቢዎቹ በመሠረተ ልማት እጥረት የተጎዱ ናቸው። ለስሙ መሃል አካባቢ ይባል እንጂ የኤሌክትሪክ ዝርጋታው እጅግ ኋላቀር ከመሆኑ በላይ እጅግ የተወሳሰበና ለአደጋም የተጋለጠ ነው። በዚህ ላይ ዝናብና የንፋስ ሽውታ ሲያገኘው በቀላሉ የሚበጠስ፤ መብራት በየአጋጣሚው የሚጠፋበት አካባቢ ነው።

> **በእነዚህ ቤቶች ገበና መደበቅ የሚባል ነገር የለም። ሰዎች የግሌ የሚሉት ነገር የለም። ምግቡም መኝታውም ሌላም ሌላም ነገሩ በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ስለሚከወን ሁሉም ነገር የአደባባይ ሚስጢር ነው**

የውሃ ማስተለላፊያ መስመሮችና የቆሻሻ ማስወገጃ ትቦዎች የተቀበሩበት ሁኔታ ኋላቀርና የጤና ችግርም የሚያስከትል ነው። አብዛኞቹ ውሃ መስመሮች ከትቦዎች ጋር መሳ ለመሳ የተቀበሩ በመሆናቸው ከመጸዳጃ ቤት የሚወጣው ፍሳሽ ከሚጠጣው ውሃ ጋር እየተደባለቀ ለከፋ የጤና ችግር ሲዳርግ የቆየበት አካባቢ ነው።

አብዛኞቹ የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች የተቀበሩት ከከተማዋ ምስረታ ጋር በተያያዘ በመሆኑ ከማርጀታቸውም ባሻገር አሁን ያለውን የሰው ቁጥር የማስተናገድ አቅም የላቸውም። በዚህም ላይ በየጊዜው በሚሰሩ ግንባታዎች አማካኝነት ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎቹ ለብልሽት ስለተዳረጉ በአግባቡ ፍሳሽን የማስወገድ አቅም ተስኗቸዋል። በዚህም ምክንያት አካባቢዎቹ በየጊዜው በሚፈነዱ መጸዳጃ ቤቶች የሚጥለቀለቁና አፍንጫ በሚሰነፍጥ ጠረናቸውም የሚታወቁ ናቸው።

እነዚህ አካባቢዎች ከችግር የተነሳ ሰዎች በግድ ይኑሩባቸው እንጂ በምንም ዓይነት መልኩ ለኑሮ የሚመረጡ አይደሉም። አካባቢዎቹ ከነግሳንግሳቸው አስታዋሽ አጥተው እና የከተማዋ ድህነት ቋሚ ዘካሪ ሆነው ዘመናትን ተሻግረው ዛሬ ላይ ደርሰዋል።

ዛሬ ግን አስተዋይ ዓይኖች ተመልክተዋቸው፤ ቅን ልቦች ዘክረዋቸው የአሮጌው አራዳ ሰፈሮች ስማቸውን የሚመጥን ዘመናዊነት ሊላበሱ ከጫፍ ደርሰዋል። ይህ አካባቢ እንደሌሎቹ የአዲስ አበባ አካባቢዎች ቀን ሊወጣለት ጥቂት ቀናት ቀርተውታል። እንደ ካሳንቺስ በለውጥ ሊታበስ፤ እንደ እንጦጦ በውበት ሊያሸበርቅ፤ እንደ አንድነት ፓርክ መንፈስን ሊያድስ የንስር ዓይኖች ተመልክተውታል፤ ብርቱ ክንዶች ዳሰውታል።

አሁን ላይ ሙሽራዋ አዲስ አበባ በአዳዲስ ፕሮጀክቶች ብቅ ብላለች። አዲስ አበባ የዓለም የዲፕሎማሲ መዲና፣ የአፍሪካ ዋና ከተማ፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የኢኮኖሚና የማኀበራዊ እንቅስቃሴ መናኸሪያ እንደ መሆኗ ይህን የሚመጥን ልማት እየተከወነላት ይገኛል።

“የኮሊደር ልማት” በሚል ስያሜ የተጀመረው ልማት በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የተሠሩ ‹‹የሚያማምሩ የልማት ሥራዎችን ማገጣጠም›› ወጥ የሆነ ገጽታ እንዲላበሱ ማስቻል ነው። እንደ ፒያሳ የመሳሰሉ በእርጅና ምክንያት ጎብጠው እየፈረሱ ያሉ የከተማዋን አካባቢዎች መልሶ ማልማት ነው።

ባለፈው ዓመት ግንቦት ጨረታው ወጥቶ የተጠናው የኮሪደር ልማቱ ወደ ትግበራ ከተገባም ቀናት ተቆጥረዋል። ልማቱ ከፒያሳ እስከ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ቦሌ ድልድይ፣ ከቦሌ ድልድይ በመገናኛ ወደ ሲኤምሲ፣ ከቦሌ ተርሚናል ወደ ጎሮ፣ ከሜክሲኮ ወደ ወሎ ሠፈር፣ እንዲሁም ከእንግሊዝ ኤምባሲ ወደ አራት ኪሎ የሚወስዱ ኮሪደሮችን የሚመለከት ነው። ሥራውም በስድስት ወራት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

እነዚህ ሥራዎች ሲከናወኑም ከተለያዩ ቦታዎች ለሚነሱ ግለሰቦች ምትክ ቦታ እንደሚሰጥ ፤ ቀደም ሲል በቀበሌ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ከቦታው በመነሳታቸው ምክንያት ለችግር እንዳይጋለጡ ምትክ የቀበሌ ቤት ወይም ኮንዶሚኒየም እንደ ምርጫቸው እንደሚሰጣቸው፤ በተመሳሳይም የግል ይዞታ የነበራቸው ነዋሪዎች ምትክ ቦታና ካሳ እንደሚያገኙ መስተዳድሩ አስታውቋል። ይህም ተግባራዊ እየሆነ ነው።

በአጠቃላይ በአምስት አቅጣጫዎች እየተከናወነ ያለው ኮሪደር ልማት ከተማዋን ከመሠረቱ የሚቀይር ነው። ከሁሉም በላይ ሥራውን በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ ለማጠናቀቅ የሚደረገው ርብርብ አግራሞትን የሚፈጥር ሆኗል። ከዚህ በመነሳትም የኮሪደር ልማቱ በታሰበለት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ መገመት አያዳግትም።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በአዲስ አበባ የተጀመረው የኮሪደር ልማት ውብና በኢትዮጵያ ልክ የሆነች ዋና ከተማን ለመፍጠር ያለመ ነው ሲሉ መደመጣቸውም አሁን ላይ እየሆነ ካለው ተጨባጭ እውነታ አንጻር ብዙም ለእሰጣ ገባ የሚጋብዝ አይደለም።

ይህም ሆኖ ግን አንዳንዶቻችን ባለማወቅ ሌሎች አውቀው ይህንን ለከተማዋ ትንሳኤ ሊሆን የሚችልን ልማት በአደባባይ ባልተገባ መንገድና ባልተገራ ቋንቋ ሲቃወሙ ይሰማል። በተለይም በሆነው ባልሆነው በተቃውሞ ቋንቋ እና መንፈስ አደባባይ ለመሙላት የሚሮጡ ግለሰቦች እና ቡድኖች ልማቱን መቃወም ከጀመሩ አረፋፍደዋል።

እነዚህ ተቃውሟቸውን ቅርስ ፈረሰ በሚል የጀመሩት ተቃውሞ ሰሚ ሲያጣ፤ ልማቱን በራሱ ወደ ማጥላላት፤ የልማቱን ባለ ራዕዮች ወደ ማጥላላት ሄደዋል። ሰሚ አላገኙም እንጂ ከዚህም አልፈው ተነስ ፤ ታጠቅ ወደሚል የጥፋት ዜማ ከገቡ ሰነባብተዋል።

እርግጥ ነው በአዲስ አበባ ከመቶ ዓመት በላይ ያስቆጠሩና የቱሪዝም መስህብ ሊሆኑ የሚችሉ ቅርሶች ባለቤት ነች። ነገር ግን ያረጀ እና ያፈጀ ቤት ሁሉ ቅርስ ነው ማለት አንድም የቅርስን ትርጉም አለማወቅ አሊያም ደግሞ ድህነትን ታቅፎ የመኖር አባዜ/እርግማን ነው።

ለመልሶ ግንባታ /እድሳት የተመረጡ አካባቢዎች ከዚህ በላይ ጎብጠው ሊቆሙ የሚችሉ አይደሉም፤ ነዋሪዎቻቸውም ከዚህ በላይ በዚህ አስቸጋሪ ሕይወት ውስጥ መቀጠል የሚችል ሰብዓዊ ስብዕና ሊኖራቸው አይችልም። አሁን ባለችው ኢትዮጵያም ከዚህ በላይ በሕይወት ሊፈተኑ አይገባም።

ይህ አካባቢ አይፍረስ፤ ሰዎች በዚህ አሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ ይኑሩ ብሎ መፍረድ ከጭካኔ በላይ ነው። አንዳንዶችም ይህን ፍረደ ገምድል ውሳኔ የሚሰጡት በአማረ ቪላ ውስጥ ሆነው ነው። አለፍ ሲልም በውጭ ሀገራት ዘመናዊ አውቶሞቢል እያሽከረከሩና በቅንጡ ቤት ውስጥ እየኖሩ ነው።

ችግሩን በሩቅ ሳይሆን አብሮ በመኖር ጭምር የሚያውቀው የኢትዮጵያ መንግሥት ዜጎቹ በዚህ አሰቃቂ ሁኔታ አይኖሩም በማለት አዲስ አበባንም ለማደስ፤ የዜጎቹንም ሕይወት ለመቀየር ቆርጦ የተነሳበት መንገድ እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው። እኛ ነዋሪዎቿም በብዙ አድናቆት የቸርነው ነው።

እኛ ብቻ ሳንሆን በልማቱ ተነስተው ወደ ሌሎች አካባቢዎች የሄዱ ነዋሪዎች ‹‹ቀን ወጣልን›› ሲሉ ተደምጠዋል። ብዙዎቹ ነዋሪዎች የቀድሞው ኑሯቸውን ከጨለማ ጋር አመሳስለው በምሬት ሲናገሩ መስማት፤ ያሳለፉትን የስቃይ ኑሮ ለመስማት ፈቃደኛ ለሆነ ሰው የልብ ስብራት የሚፈጥር ነው።

በአንዲት ክፍል ለዘመናት ተጨቁነው የኖሩት እነዚህ ምስኪን ዜጎች ዛሬ ገበናቸው ተከቷል። የጋራ መኖሪያ ቤትም ሆነ ተገጣጣሚ ቤቶችን የመረጡ ዜጎች እንደ ሰው ለመተኛት፤ በዘመናዊ ሻወር ለመታጠብ፤ በሁለት በሶስት ክፍል ውስጥ ለመምነሽነሽ ፤ በንጹህ መጻዳጃ ለመጠቀም በቅተዋል።

የኮሪደር ልማቱ ሰፊ አካባቢን የሚሸፍን በመሆኑ ልማቱ ገና የሚቀጥል ነው። የተጀመረው ልማትን በፍትሃዊነት ለዜጎች የማዳረስ ጥረት እስከ መጨረሻው ሊቀጥል፤ በልማቱ የሚነሱ ዜጎች ያልተገባ እንግልት እንዳያጋጥማቸው ሥራዎች በጠንካራ ዲሲፕሊን ሊመሩ ይገባል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እንዳሉት ሌብነትና ኢፍትሃዊነት ካለ ይህ ግዙፍ ፕሮጀክት ዋጋ ቢስ ስለሚሆን ፤ ፕሮጀክቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሌብነትንና ኢፍትሃዊነትን መዋጋት ፕሮጀክቱን የሚያስተባብሩ ኃላፊዎች ዋነኛ ትኩረት ሊሆን ይገባል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን

ዓርብ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# 4ኛው ዙር የአዲስ አበባ ብስክሌት ክለቦች ቻምፒዮና እሁድ ይካሄዳል

ዓለማየሁ ግዛው

በየዓመቱ የሚካሄደው የአዲስ አበባ ክለቦች፣ የታዳጊዎች፣ የግል ተወዳዳሪዎችና የቀድሞ ብስክሌተኞች ቻምፒዮና እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ውድድሩ ሶስተኛ ሳምንቱን የያዘ ሲሆን በሰሚት፣ በአዲሱ ገበያና በቴዎድሮስ አደባባይ ለስምንት ሳምንታት ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡

በዘንድሮው ቻምፒዮና በዋናነት አራት ክለቦች እየተፎካከሩ ይገኛሉ፡፡ ኢትዮ ኤሌክትሪክ፣ ጋራድ፣ አዲስ አበባ ፖሊስና የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ናቸው፡፡ የግል ተወዳዳሪዎች፣ ታዳጊ ፕሮጀክቶችና የቀድሞ ብስክሌተኞች በውድድሩ ድምቀትን መፍጠር ችለዋል። በቻምፒዮናው በርካታ ስፖርተኞች እየተካፈሉ ሲሆን በታዳጊ ፕሮጀክቶች ደረጃ 35 ብስክሌተኞች፣ 39 የግል ተወዳዳሪና አዋቂ ማውንቴን ብስክሌተኞች፣ 16 በማውንቴን ሴቶችና 20 የሚደርሱ የቀድሞ ብስክሌተኞ እንዲሁም 25 የክለብ ተወዳዳሪዎች ጠንካራ ፉክክር እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

ውድድሩ መካሄድ የጀመረው መጋቢት 1/2016 ዓ.ም ሲሆን ሶስተኛ ሳምንቱን አስቆጥሯል፡፡ ሚያዝያ 20/2106 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅም የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን አስታውቋል፡፡ በዚህም መሰረት ቀሪ የአምስት ሳምንታት ውድድሮች በጉጉት የሚጠበቁ ሆነዋል፡፡ ባለፍው እሁድ በተካሄዱ የሶስተኛ ሳምንት ውድድሮች በሁሉም የፉክክር አይነቶች በከፍተኛ ፉክክሮች ታጅበው ተጠናቀዋል፡፡

በኮርስ ብስክሌት በክለቦች መካከል በ28 ዙሮች በተደረገው ፉክክር ፍራኦል ወልደኪዳን ከኢትዮ ኤሌክትሪክ



የከተማዋ የብስክሌት ቻምፒዮና በጠንካራ ፉክክር እየተካሄደ ይገኛል፣

በቀዳሚነት አጠናቀል፡፡ ፉአድ ሻሚል ደግሞ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ሁለተኛ ሆኖ ውድድሩን ሲፈፅም፣ ሰለሞን ዓለሙ በተመሳሳይ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ሶስተኛ በመሆን ውድድሩን ጨርሳል፡፡ በዕለቱ ፉክክርም ብስክለተኞቹ በሰዓት 41.37 ኪሎ ሜትር በመጋለብ ውድድራቸውን እንደጨረሱ ታውቀል፡፡

በአዋቂዎች መካከል 21 ብስክሌተኞችን ባፋለመው ውድድር እሱባለው አማረ 1ኛ፣ የአብስራ ካሳሁን ሁለተኛ እና ዳግም ታሪኩ 3ኛ በመሆን አጠናቀዋል፡፡ በቀድሞ ብስክሌተኞች መካከል የተካሄደውን ውድድር ችኖ ሮልሰ 1ኛ፣ ወልደወሰን አገሬ 2ኛና አንተነህ ተሾመ 3ኛ በመሆን ጨርሷል።

ውድድሩ በተለያዩ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች እየተካሄደ ሲሆን እንደየ ፉክክር አይነቱ የሚሸፍነው ርቀትም የተለያየ ነው፡፡ የመጀመርያው ውድድር ሰሚት የተባበሩት አካባቢ ነበር የተካሄደው፡፡ የሁለተኛ እና ሶስተኛ ሳምንት ውድድር ደግሞ አዲሱ ገብያ አካባቢ ከሚገኘው ጺዮን ሆቴል እስከ ጉለሌ እጽዋት ማእከል ባለው መንግድ ላይ ተካሂዷል፡፡

ብስክሌት ጋላቢዎቹ አንድ ቦታ ብቻ እንዳይለምዱና የመወዳደርያ ስፍራን ምቹ ለማድረግ የተለያዩ የማዘውተርያ ስፍራዎች ማግኘት እንደሚኖርባቸው ታስቦ በተለያዩ ቦታዎች ውድድራቸውን እያከናወኑ እንደሆነም ፌዴሬሽኑ ጠቁሟል፡፡ አዲሱ ገብያ አካባቢ ከፍታና ቀዝቃዛ፣ ዳገታማና ቁልቁለታማ በመሆኑ ለውድድር ተመራጭ አድርጎታል፡፡ ሌላው ውድድሩ የሚካሄድበት ስፍራ ቴዎድሮስ አደባባይ እንዲሁ ቁልቁለትና ዳገት ያለው እንደሆነና ለስፖርተኞቹ የተለያዩ መሰናክሎችን ማለፋቸው በቀጣይ ከተማ አስተዳደሩንና ሀገራቸውን ወክለው ሲሳተፉ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ እገዛ ያደርጋል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

በዚህም መሰረት ታዳጊዎች እስከ 16 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ግልብያን ያደርጋሉ፡፡ የቀድሞ ብስክሌተኞች እስከ 20 ኪሎ ሜትር ይጋልባሉ፡፡ አዋቂ የማውን ብስክሌት ጋላቢዎች እስከ 30 ኪሎ ሜትር የሚነዱ ሲሆን ክለቦች ደግሞ 95 ኪሎ ሜትር ሚጋልቡ ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ብስክሌት ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ ተረፈ፣ ክለቦች በዓመቱ መጀመሪያ የአቋም መለኪያ ውድድር በማድረግ አቋማቸውን ከፈተሹ በኋላ ይህ ቻምፒዮና ትልቁ ውድድራቸው መሆኑን ተናግረዋል። ተዳዳሪዎቹ በተለያዩ ውድድሮችና ካታጎሪዎች ከተማ አስተዳደሩን ወክለው የመሳተፍ እድል እንዳለቸውም ጠቅሰዋል፡፡ ሁሉም ተወዳዳሪዎች በደንብ ዝግጅት አድርገው እየተሳተፉ በመሆኑ ደማቅና ጥሩ ፉክክር እየተደረገበት እንደሆም አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም በውድድሩ ጥሩ ውጤትና አፈጻጸም ያላቸው ስፖርተኞች በብሔራዊ ፌዴሬሽን ደረጃ ሀገርን ወክለው እንዲሳተፉ ምልመላ ተደርጎ የሚላክበት ሁኔታም እንዳለም የፅህፈት ቤት ሀላፊው ጠቅሰዋል፡፡ በመሆኑም ተወዳዳሪዎች በከታማው ውድድር ተገድበው የሚቀሩ ብቻ ሳይሆን ሀገርን የመወከል እድል ሊያገኙ ይችላሉ። ቻምፒዮናው ስፖርቱ እንዲስፋፋ ሰልጣኞች ውድድር በማግኘት ጠንካራ ተፎካካሪና ውጤታማ እንዲሆኑ በር ይከፍታል፡፡ ፌዴሬሽኑም ስፖርተኞች በጥሩ ስነምግባር ተወዳድረው ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም ከክለቦች፣ ተወዳዳሪ ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞችና ዳኞች ጋር በውድድር ድንብ ዙሪያ ውይይቶችን በማድረግ ከሚገኙ ሃሳቦች ተነስቶ በማጽደቅ ወደ ውድድር ተገብቷል፡፡